ሚያዝያ፤ 24፤ 2011

# የሃገራችን ፖለቲካዊ ሁኔታና ቀጣይ እርምጃዎች

## 1. መግብያ

በሃገራችን ኢትዮጵያ የነበረው የኣስተዳደር ዘይቤ ከተለወጠ ኣንድ ኣመት ሞልቶታል። በህገመንግስቱ መሰረት ደግሞ በየኣምስት ኣመቱ የሚደረገው ምርጫ ኣንድ ኣመት ቀርቶታል። ባለፈው ኣንድ ኣመት የፖለቲካ ምህዳሩ መስፋቱ፤ የፖለቲካ እስረኞች መፈታታቸው፤ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል መልካም ግኑኝነት መፈጠሩና የጦርነት ዳመና መቀንጠጡ ጥሩና የሚደገፉ ስራዎች ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ ኣንድ ኣመት ለቀረው ምርጫ ግልፅና የማያሻማ ውሳኔ ኣለመኖሩ በዚህ መሰረት በቂ ዝግጅቶች ኣለመካሄዳቸው በገዢው ፓርተ ውስጥ ባሉት የፖለቲካ ድርጅቶች መሃከል የሃሳብና የኣሰራር ልዩነቱ ጤናማ መሆኑን ጥየቄ ውስጥ መግባቱ ኢኮኖሚው በሚያሰጋ ሁኔታ ውሰጥ መሆኑ ዜጎች በሚልዮኖች መፈናቀላቸው በማንነታቸው ምክንያት ለከፍተኛ ጥቃት (የሞት የንብረት ውድመት) መዳረጋቸው፤ ሰላምና መረጋጋት የህግ የበላይነት በሃገሪቱ ኣለመስፈኑ፤ የወጣቶች የስራ ኣጥነትና የፖለቲካ ተሳትፎ ጊዜውን ጠብቆ የሚፈታበት ተስፋ ኣለመኖሩ፤ በጠቅላላ የተጀመረው የሽግግር ሂደት በተሻለ ውጤት ለማጠናቀቅ የሚያስችል ፍኖተ ካርታ ኣለመኖሩና  ይባስ ብሎም ኣሰፈላጊነቱ ጥያቄ ውስጥ መግባቱ ኣገራችን እጅግ ኣሳሳቢ በሆነ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ እንድትገኝ ኣድርጎኣታል።

በዚህ ላይ ደግሞ የተቃዋሚው የፖለቲካ ጎራ እጅግ የተበታተነ ከመሆኑም በተጨማሪ ብዙዎቹ እንደኣማራጭ በገልፅ ለህዝብ ያቀረቡት ሃገራዊ የፖለቲካ ፕሮግራም፤ የምርጫ ማኒፌስቶ መኖሩን ኣናውቅም። እነዚህ ሁኔታዎች በድምር ሃገራችንን በከፍተኛ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ እንድትገባ ኣድርጓታል። እነዚህ (የተጠቀሱትና ያልተጠቀሱም ይኖራሉ) እስትራተጂካዊ ኣደጋዎች ሃገራችንን ወደ ማትወጣው ማጥ ሊከቷዋት ይችላሉ። ስለዚህ በቀረው ኣጭር ጊዜ በከፍተኛ መረባረብ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ኣቅጣጫና ሃገራዊ ኣቅማችን ያገናዘበ የስራ ቅደም ተከተል መያዝ ይገባል የሚል ሃሳብ ኣለን። የዚህ ፅሁፍ ኣላማም በዚሁ በሃገራችን ጉዳይ ላይ በሚደረጉ ውይይቶችና መፍትሄ የማፈላለግ እንቅስቃሴ ኣስተያየታችን ለመስጠት ነው።

## 2. መነሻችን

### 2.1. ሃገራዊ ሁኔታ

ሃገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበት የፖለቲካ ሁኔታ ስንል በቅርቡ (ከ2008ዓ/ም) በኃላ ያለውን ይበልጥ ደግሞ ባለፈው ኣንድ ኣመት ያለውን ሁኔታ መነሻ በማድረግ ነው የምንመለከተው። ከቀጣይ

እርምጃዎቻችን ኣንፃር ዋናው ጉዳይ ይህ በመሆኑ። ያለፍንበት ታሪካዊ ጉዞ ለኣሁኑ ሁኔታችን ተፅእኖ የለውም ብለን ሳይሆን (የተለያዩ ትርክቶች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ) ይህ ፅሁፍ የታሪክ ፅሁፍ ባለመሆኑ ዋናው ትኩረታችን ኣሁን ከደረስንበት የፖለቲካ ምእራፍ በሃገራችን ሰላምና ዲሞክራሲ ከማስፈን ኣንፃር (እንዴት ብንቀጥል ይሻለናል በሚለው ሃሳብ) ላይ ኣስተያየታችን ግልፅ ለማድረግ ነው።

ከኣንድ ኣመት ገደማ የመጣው ለውጥ ከመከሰቱ በፊት በኢህኣዴግ የሚመራው የሃራችን የፖለቲካ ኣስተዳደር የፌደራል ስርኣቱ ከሚጠይቀውና የስርኣቱ መሰረት ከሆነው በተለይ ደግሞ እንደሃገራችን በመሰሉ ብዙሃነትን ማስተናገድ በሚገባቸው ሃገራት የግድ መኖር የነበረበትን ሰፊ ዲሞክራስያዊ ምህዳር በጣም እየጠበበ በህገመንግስቱ በተቀመጡ የቡድን ሆነ የግለሰብ፣ ኢኮኖምያዊና ማህበራዊ መብቶችን ኣጋጣሚው ሲከሰት እየደፈጠጠ ፖለቲካዊ ልዩነቶችን በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ ሳይሆን በፀጥታዊ ኣስተዳደራዊ መንገድ እየፈታ ህብረተሰቡን አሸማቆና ኣድረባይ ኣድረጎ ማስተዳደርን እንደ ፖሊሲ ሲጠቀም የነበረ ኣስተዳደር ነበር። በህገመንግስቱ የተቀመጠውን ፌደራላዊ ኣስተዳደር ኣሃዳዊ ኣስተዳደር በሚመስል ሁኔታ ኣማክሎ በክልሎች ጉዳይ ጣልቃ እየገባ ሲያስተዳድር የነበረ ነው። ለኢህኣዴግ ዲሞክራሲ በተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎች መሃከል የሃይል ሚዚናቸውን መሰረት ያደረገ ድርድር ከዚህ ኣልፎ ደግሞ ተኣማኒነት ባለው ህዝባዊ ምርጫ የሚሰጥ የህዝብ ውሳኔ ውጤት ሆኖ በቀጣይነት እያደገ ስር እየሰደደ የሚሀድ ሂደት ሳይሆን ሰጪና ተቀባይ ያለው፣ ሰጭው ለሱ የሚጠቅመውንና የፈቀደውን የሚሰጥ ተቀባይ ደግሞ ኣሜን ብሎ የተሰጠውን ያህል በቻ ተቀብሎ በፀጋ የሚኖር ኣድርጎ የሚያስብ ኣስተሳሰብ ነው ሲሰራበት የነበረው። በፅሁፍና በንግግር የሚባለው ሌላ ሊሆን ይችላል በተግባር የታየው ግን የተገለፀው ነው። ይህ ደግሞ መቀጠል ኣልቻለም የለውጡ መነሻ ይህ ነው።

ይህ ከላይ የተገለፀው ሁኔታ ህብረተሰቡ ውስጥ በፍትህ መጓደል ወይም ኣድልዎ የመልካም ኣስተዳደር እጦት፣ ፍትሃዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት፣ መብቱን ለመጠየቅ የሚፈራ የተሸማቀቀ ህብረተሰብ ራሳቸውን ከህግ በላይ ኣድርገው እንደፈለጋቸው የሚያደርጉ የመንግስት የስራ ኣስፈፃሚ ኣካላትን መረን የለቀቀ ለፓርቲው ታማኝ ነን እስካሉ ድረስ ጠያቂ የሌላቸው በየደረጃው የተሰገሰጉ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ለመንግስትና ለህዝብ ሃብት ምዝበራና ብክነት ምክንያት ሆነዋል። ፓርቲና መንግስት ልዩነታቸው ጠፍቶ ኣንድ የሆኑበት የመንግስት መሰረታዊ ተቋማት (ህግ ኣውጭው፣ ህግ ተርጓሚውና ስራ ኣሰፈፃሚው) በስራ ኣስፈፃሚው ብቻ እንደፈለገው የሚዘወሩበት የህዝብ ተመራጮች ለህዝባቸው ባላቸው ተቆርቃሪነትና ተጠያቂነት ሳይሆን ለፓርቲው ባላቸው "ታማኝነት" የህዝብ ውክልና ኣግኝተዋል እየተባለ የሚመረጡበት ከዚህ ሲያልፍም ምርጫ የሚጭበረበርበት ሁኔታ ውሰጥ ነው የነበረነው። ይህ መለወጥ ነበረበት፣ የለውጡ ኣስፈላጊነትም ከዚህ ኣነፃር ነው መለካት ያለበት። <u>ውጤቱም ይህንን ሁኔታ ማስተካከል መሆን አለበት ብለን እናምናለን።</u>

ለውጡ የመጣው በህብረተሰቡ ውስጥ መጠኑና ግፊቱ ቢለያይም በሁሉም የሃገራችን ኣከባቢዎች በተቀሰቀሰ የህዝብ ቁጣ ነው።ጠንካራው የህዝብ ኣመፅ በኦሮምያና ቀጥሎም በኣማራ ክልለ የነበረ ቢሆንም ትግራይ ውስጥና ሌሎች ክልሎችም ወስጥ የነበረው የህዝብ ቁጣና በተለይ የወጣቶች ተቃውሞ ቀላል ኣልነበረም። ይህ የህዝብ ቁጣና ምሬት ገዢው ፓርቲ ኢህኣዴግንም እራሱን እንዲፈትሽ በማስገደድ በፓርቲ ውሰጥም የለውጥ ኣሰፈላጊነትና ለውጥ ለማምጣት የሚፈልግ ሃይል እንዲወጣ ምክንያት ሆነ። ይህ የህብረተሰብ ከፍተኛ ተቃውሞና በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረው የለውጥ ሃይል በቅንጅት ለውጡን ኣመጣ። ለውጡ የነበረውን መንግሰት በሃይል፤ በኣመፅ ጠራርጎ ለማስወገድ በሚፈልጉ የኣመፅ ሃይሎችና ለውጡን ከውሰጥ ለማምጣት የመንግሰትን ስልጣን በመቆጣጠር ለማምጣት በሚፈልጉ ሃይሎች በቅንጅት የመጣ ነው። ይህ ለውጡ የመጣበት ሁኔታ እስከኣሁን ድረስ ለውጡን በማስተዳደር (manage) ማድረግ ላይ ተፅእኖው ይታያል። በሁለቱም ሃይሎች መሃከል ውጥረት ያለ ይመስላል። ኣሁንም የለውጡ ኣካሄድና ሊያስመዘግባቸው በሚፈለጉ ውጤቶች ላይ የሁለቱም ሃይሎች ፈላጎቶች ውጥረት ውሰጥ የሉ ይመስላል። የዚህ ዋና መገለጫው በየስብሰባው የሚሰነዘሩት ሃሳቦችና በተለይ ደግሞ ኢህኣዴግ ውስጥ ያለው ሁኔታ ነው።

በሃገር ደረጃ የተቀሰቀው ቁጣና የለውጥ ፍላጎት በኣመፅና በነውጥ ቢጠናቀቅ ኖሮ በሃገራችን ኣንዣብቦ የነበረው የፖለቲካ ስጋትና ይህ ሊያስከትል ይችል የነበረው ኣደጋ እጅግ ከፍተኛ ይሆን ነበር። ሃገራችን ኣሁን ባለችበትና ከለውጡ በፊት በነበሩት ጊዜያት በነውጥ ስልጣን ላይ የነበረውንና ያለውን ኣስተዳደር መጠራረግ ተሸክማ እንደሃገር መቀጠል ትችል ነብር ወይ ተብሎ ሲጠየቅ መልሱ እጅግ ኣጠራጣሪ ነው። ኣስተዳደሩን በጠቅላላ በነውጥ ከመጠራረግ በመለስ በመጣው ለውጥ እንኳን እንደሃገር ሁኔታውን ተሸክመን ማለፍ እየከበደን መሆኑ በግልፅ እየታየ ነው። ነውጥ ቢከሰት የመንግስት መዋቅሮች የኢኮኖሚ ኣውታሮች በከፍተኛ ደረጃ ይወድሙ ነበር ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ደም መፋሰስና ንብረት መውደም ይደርስ ነበር። ሃገር እንደ ሃገር የመቀጠል እድሉ የጨለመ ይሆን ነበር። ይህ ሳይሆን መቅረቱና ለውጡ በመጣበት መንገድ መከሰቱ (የማይቀር ለውጥ ስለነበረ) እንደየተሻለ ሁኔታ ማየቱ ተገቢ ነው። ይህ ሲባል ለውጡ በመጣበት መንገድም የጠፋ ሂወትና የወደመ ንብረት፤ በህዝብ ላይ የደረሰ የኣካል ይሁን የስነኣምሮ ጥቃት ኣልነበረም ማለት አይደለም። ኣሁንም ቢሆን ተፈጥሮ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ኣያሳስብም ማለትም ኣይደለም። በጣም ኣሳሳቢ ነው። ግን ኣሁን በኣንድ ሃገር ውስጥ ሆነን የመንግስት መዋቅር ጠቅልሎ ሳይፈራርስ የሂወትና የንብረት ጉዳቱን ተሸክመን ችግሩን ለመፍታት እየሞከርን እንገኛለን። ይህ ቀላል ጉዳይ ኣይደለም።

ሃገራዊ የፖለቲካ ቀውሱ ኣሁን ካለበት ደረጃ የባሰ እንዳይሆን ኣስተዋፅኦ ያደረጉ ምክንያቶች ኣሉ። በኢትዮጵያ ህዝቦች የነበረው፤ ያለው፤ የረጅም ጊዜ ኣብሮ መኖር መከባበር በሃይማኖት በባህል በጋብቻ በሌሎችም ብዙ ገመዶች የተሳሰረ መሆኑ የኣደጋውን መጠን ከተከሰተበት በላይ እንዳይሆን ወደ ጠቅላላ

የርስበርስ መፋጀት እንዳያድግ ኣስተዋፅኦ ኣድርገዋል። መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች በበጎም በክፉም ጊዚያት በጋራ የሰራቸው፣ የተጋፈጣቸው፣ ሃገራችንን እንደኣንድ ሃገር ለረጅም ጊዜ እንድትቆይ ያደረጉ ክስተቶች፣ በህዝቡ ውስጥ የፈጠሩት ሰብኣዊነትና ኣንድነት፣ ኣደጋውን በእጅጉ ቀንሶታል። ችግሮች በተፈጠሩበት ኣከበካቢ ገሚሱ ሲገድል ገሚሱ ያድናል። ሌላው ሲዘርፍ ገሚሱ ይከለከላል። ይህ ሁኔታ ባይኖር ኖሮ ሲነዛ በነበረው የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ህዝቡ እርስ በርሱ ይተላለቅ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይ ህዝብ ኣደጋውን ካስተዋለ በኋላ በውስጡ ያሉትን ችግሮችና ልዩነቶች ኣቆይቶ እንደህዝብ እየመጣብኝ ነው ብሎ ያመነበትን ኣደጋ ለመከላከል በኣንድነት በፅናት ቆመዋል። የትግራይ ህዝብ ይህንን በማድረግ እስካሁን ለኣደጋው ሳይጋለጥ ዘልቋል። ሌላወ እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ <u>የሌለበት ትልቅ ጉዳይ በጠቅላላው የሃገርን ሰላም በማስጠበቅ በኩል ትልቅ ድርሻ የነበረው የሃገር መከላከያ ሰራዊት ነው።</u> ይህ የመንግስት ተቃም በተቻለ መጠን ህገመንግስቱን መሰረት በማድረግ ችግሮች በተከሰቱበት ኣከባቢዎች እየገባ ፀጥታ እንዲከበር ህዝብ እንዲረጋጋ ሰላም እንዲመለስ ትልቅ ኣስተዋፅኦ ኣድርገዋል። የሰራዊቱ ኣባላት በተቻለ መጠን ከወገንተኝነት የፀዳ ሃገርንና ህገመንግስትን ያስቀደመ በጥሩ ዲሲፕሊን ለሰሩት ስራ ሊመሰገኑ ይገባል። አገሪቱንም ከባሰ ጉዳትና መፈራረስ ታድኋል ብለን እናምናለን።

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ሁኔታዎች በሃገራችን የተከሰተውን ቀውስ ከደረሰበት ደረጃ እንዳይባባስ ትልቅ ድርሻ የተጫወቱ ክስተቶች በህዝቦች ያሉ እሴቶችና የመከላከያ ሰራዊታችን ለኢትዮጵያ ህዝቦች ፍላጎትና ለህገመንግስቱ ታማኝ መሆን ለወደፊትም ሃገራችን ከፖለቲካው ቀውስ ለመውጣት በምናደርገው ጥረትም በተገቢው መንገድ ከተጠቀምንባቸው ከፍተኛ ኣስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ብለን እናምናለን።

ኣሁን የምንገኝበት ሁኔታ ስናይ ደግሞ የሃገሪቱን የፖለቲካ ስልጣን እከኣሁን ድረስ ተቆጣጥሮ የነበረው ኢህኣዴግ ውሰጥ ያሉት ኣራቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ የኣስተሳሰብና የኣሰራር ኣንድነት የጠፋ መሆኑን ሃላፊዎቹ በየኣጋጣሚው ሲገለፁ እንሰማለን። ጠቅላላ ጠፍተዋል እንዳንል ኣንዳንዴ ብቅ እያሉ የተለወጠ ነገር የለም ስለሚሉንና ኣሁንም በኣህኣዴግ ገዥ ፓረቲነት ስም ሀገራችን እየተዳደረች ስለኣለች ነው። ከዚህ ኣልፎ ግን ድርጅቱ የቆመላቸው ኣስተሳሰቦች እንደ ኣብዮታዊ ወይም ልማታዊ ዲሞክራሲ ብሄር ብሄረሰቦችን መሰረት ያደረገው ፌደራላዊ የፖለቲካ ኣስተዳደር ኣወቃቀር፣ የመንግሰት በኢኮኖሚ እድገት ያለው ሚና ላይ ልዩነቶች እንዳሉ በግልፅ ባለፈው ጉባኤ ታይተዋል። ከዚህ በተጨማሪም የፖለቲካ ድርጅቶቹ የነበራቸውን ድርጅታዊ ኣሰራር ማለትም ጊዜውን የጠበቁ ስብሰባዎችና በዚህ መሰረት የሚወሰኑ ውሳኔዎች እንደተለመደው እየሄዱ ያሉ ኣይመስሉም። በኣንዳንድ

ውሳኔዎች ላይ ልዩነቶች ኣሉ (ለምሳሌ በማንነት እና የወሰን ማካለል ኮምሽን ጉዳየ ላይ፤ በፓርቲው ውህደት ላይ)። ጠቅለል ባለ መልኩ ድርጅቶቹን ኣስተሳስረው የነበሩት የፖለቲካ ኣስተሳሰቦች በተለይ ኣሁን በስራ ላይ ያለው ህገመንግስትና ከዚህ የሚመነጨው የኣስተዳደር ኣከላለል፤ ድርጅቱ ሲከተለው የነበረው የፖለቲካል ኤኮነሚ ኣስተሳሰብ (developmental state)፤ ውስጣዊ ኣሰራራቸው ላይ፤ ችግሮች ኣሉ። ይህ ማለት ስትራተጅክ ኣመራሩ ውስጥ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮኣል ማለት ነው።

በዚህ ሁሉ መሀል ደግሞ በገዥ ፓርቲና በውስጡ ባሉ ድርጅቶችም ግልፅ ሆኖ የወጣ ለህዝብ በይፋ የተነገረ የፖለቲካ ኣስተሳሰብ የለውጥ ኣጀንዳና ኣካሄድ የለም። በኢህኣዴግ ውስጥ ሆነው የቆየውን ኣስተሳሰብ የሚቃወሙ ድርጅቶች በኣንዳንድ ኣጋጣሚወች ተቃውሞኣቸውን ይገልፃሉ እንጂ በተደራጀ መንገድ በሌላ ኣማራጭ ሃሳብ ለመተካት እንደሚፈልጉ በግልፅ ኣልወጣም። ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ በንቃት ለሚከታተለው የህብረተሰብ ክፍል (ኣሁን ደግሞ ይህ ክፍል ቁጥሩ እጅግ ተበራክተዋል) በየኣጋጣሚው ከሚደመጡ የሃላፊዎች ንግግሮች ብቻ እንዲገምት ኣስገድዶታል። ይህ በሚገባ ታስቦበት የሚደረግ የሚመስል የግልፅነት መጓደል (deliberate ambiguity) ኣሁን በሃገራችን ላለው የፖለቲካ ኣለመረጋጋት እያስከተለ ያለው ጉዳት ከፍተኛ ነው።

ለውጡን ተከትሎ በውጭ ሃገር የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሃገራቸው ገብተዋል። ይህ ኣሰራር ህግና ስርኣት የተከተለ ባይሆንም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሃገር ቤት መግባታቸው የሚደገፍ ነው። በሃገር ውስጥ ሆነው ሲጋጥሙዋቸው የነበሩ ችግሮች እየቻሉ ሲታገሉ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሁኔታው ኣሁን ተመቻችቶላቸዋል። ይህ ሁኔታ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማእከሉ ሃገር ውስጥ እንዲሆን ኣድርጎታል። ይህ ጥሩና የሚደገፍ ነው። እነዚህ ሃገር ውስጥም ይሁን በውጭ ሃገርም ሆነው ሲታገሉ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራም ይሁን በተናጠል በሚገባ የታሰበበትና የተጠናቀረ በሃገራችን መከተል ያለብን የሃገረ መንግስት ግንባታ (state building) ኣቅጣጫ የሚያሳይ ኣስተሳሰብና የኣሰተዳደር ኣወቃቀር በግልፅ ለህዝብ በይፋ ኣልወጣም። ይህ በዋናነት በጥላቻ ፖለቲካ ብቻ ተዘፍቆ የነበረው የፖለቲካ ሃይል ከነበረው ኣዙሪት ወጥቶ የተለየና ረጅም ርቀት ያማተረ የሃገረ መንግስት ግንባታ (state building) ፕሮግራም ኣውጥቶ ለህዝብ ይፋ ማድረግ ይጠበቅበታል። ከዚህ ኣንፃር ኣሁንም በተለያዩ ኣጋጣሚዎች የፓርቲ ሃላፊዎች ከሚሰጡዋቸው የተቆራረጡ መግለጫዎች በዘለለ የሃገረ መንግስት ግንባታ እንቅስሳሴው የሚመራበት ኣቅጫጫ፤ በሃገር ውስጥ ሰላም ለማስፈን ሚያስችል የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ኣሁን ከችግር የሚወጣበት በቀጣይነት ደግሞ እድገት የሚያሳይበት፤ የሃገር ኣሰተዳደር ስርኣቱ በጥልቀትና በስፋት ተዘርዝሮ የፓርቲ ፕሮግራምና የምርጫ ማኒፌስቶ ሆኖ ኢህኣዴግ ኣሁን እየተከተለው ካለው የተለየ መሆኑን በማሳየት ለመራጩ ህዝብ መቅረብ ኣለበት። ይህንን እሰከኣሁን ድረስ ኣላየንም። እዚህም ላይም ከፍተኛ የሰትራተጂክ ኣመራር ችግር ያለ ይመስለናል።

ይህ ሁኔታ በድምር የሚያሳየን የህዝቦች የለውጥ ፍላጎቶት ከፍተኛ እንደሆነ ግን ለውጡ እንዴት ይቀጥላል? ምን የተሸለ ኣማራጭ ይመጣል? ወይም ካለፈው የፖለቲካ ኣስተዳደር ምኑ ይሻሻላል? የሚለው ህዝብን በሚያሳምን መንገድ በግልፅ ኣለወጣም። ይህ ደግሞ ከፍተኛ የፖለቲካ ኣለመረጋጋትና ቀውስ ኣስከትለዋል። ከባድ የሰላምና መረጋጋት እጦት ኣለ። ህዝቦች እየተፈናቀሉ ነው። በማንነት ጥያቄ ላይ ተመስርተው እርስ በርሳቸው እየተፋጁ ነው ። ሁኔታው ለዚህ መፍትሄ የሚያስቀምጥ ስትራተጂያዊ ኣቅጣጫ ኣስቀምጦ በፍጥነትና በከፍተኛ ሃላፊነት፤ በውጤታማነት መንቀሳቀስን ይጠይቃል።

ኣሁን ያለው የፖለቲካ ቀውስ ቀስ በቀስ የሀገራችንን ኢኪኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳው ነው። የውጭ ሃገር ባለሃብቶች ሃገራችን ውስጥ መዋእለ ንዋየቸውን ለማፍሰስና ራሰቸውን ጠቅመው ሃገራችንና ህዝባችን ለመጥቀም የነበራቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት እንደቀነሰ መገመት ይቻላል። የሃገር ውሰጥ ባለሃበቱም ኣዳዲስ  ስራ ፈጣሪ ኢንቨስተመንት ማድረግ ይቅርና ቀደም ብለው በስራ ላይ የነበሩ ድርጅቶች በየወጭ ምንዛሪ እጥረት ከፍተኛ ችግር ውሰጥ እንደሆኑ ይታወቃል። በመንግስት ደረጃም ትላልቆቹ ፕሮጀክቶች ባለፈው ኣመት የስራ እንቅስቃሴኣቸው እዲያቆሙ ተገደዋል። ኮንስትራክሽን ኢንዳስትሪው (በኣሁኑ ጊዜ ትልቁ ስራ ፈጣሪ) በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዳለ ይታወቃል። እነዚህ የኢኮኖሚ ችግሮች ቀስ በቀስ ወደ ፖለቲካ ችግር ይቀየሩና የስራ ኣጡ ብዛት፤ የዋጋ ንረቱ፤ እቃዎች ኣለመገኘት፤ የኑሮ ውድነቱ፤ ተጠራቅመው የፖለቲካ ቀውሱን ይበልጥ በማባባስ ለመመለስ ኣስቸጋሪ ወደ ሆነበት ደረጃ እንዳይገፋት ማሰብ ያስፈልጋል። እነዚህ ሁኔታዎች በተናጠልና እርስ በርሳቸው በመደጋገፍ የሚፈጥሩት ሁኔታ ሃገራችንን ወደ ከፍተኛ ቀውስ ውሰጥ እየከቷት ባለንበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

በዚህ የሽግግር የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ባለንበት ሁኔታ የውጭ ሃይሎች ጣልቃ ገብነት በተለይ በኤርትራው መሪ ፕረዚደንት ኢሳያስ ኣፈወርቂ ደላላነት ከመሀከለኛ ምስራቅ ሃገሮች ጋር የሚደረገው ግኑኝነትና ፕረዚደንት ኢሳያስ በሃገራችን ጉዳይ ላይ ያላቸው ኣሉታዊ ሚና የራሳችንን ችግሮች በራሳችን እንዳንፈታ ሌላ ተጨማሪ ነገሩን የመያባብስ ሁኔታን እየፈጠረ ነው። እዚህ ላይ መግለፅ የምንወደው ጉዳይ በኤርትራና ኢትዮጵያ መሃከል ሰላም መውረዱ በተለይ ደግሞ በሁለቱ ወንድማማች ህዝቦች መሀከል ሰላም መፈጠሩና የህዝብ ለህዝብ ግኑኝነት ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንዲጎለብት ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን ከልብ እንደግፋለን። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንግስታቱ የሚደረገው ግኑኝነትና ስምምነት ደግሞ በየደረጃው ጊዜውን እየጠበቀ የሚመለከታቸው የመንግሰት ኣካላትና የፖለቲካ መሪዎች እየተወያዩበት፤ እያመኑበት፤ ውሳኔ እየሰጡበት፤ ከዚህ ቀጠሎም ጊዜውን ጠበቆ ለሀዝብ የሚገለፅበት ኣካሄድ መከተል ይገባል። ከሁሉም በላይ የውጭ ሃይሎች ጣልቃገብነት የሃገራችንን የኣሁን ይሁን

የወደፊት ሃገራዊ ጥቅሞችን የማይጎዳና ኣደጋ ውስጥ የማይከት ኣሁን ካለንበት የፖለቲካ ቀውስ ደግሞ ተጨማሪ ቀውስ የማይፈጥር በህዝቦች ንቁ ተሳትፎ በእርጋታና እየተጠና የሚደረግ መሆን ይኖርበታል።

ከፍ ሲል ሲገለፁ ከነበሩ ችግሮችና ተግዳሮቶች በተጨማሪ መታሰብ ያለበት ጉዳይ የሃገራችን ተቋማዊ መዋቅር፤ ኣሁን በለውጡ ምክንያት (በሽግግሩ ዘመን) መዋቅሩ እንዲሸከም እየተገደደ ያለውን ስራ ጠቅላላውን ሳይፈራርስ መሸከም ይችላል ወይ የሚለው ጉዳይ ነው። የሃገራችን መንግስታዊ መዋቅሮች በየጊዜው እየተጨፈለቁና እየፈረሱ እንደገና እንዳዲስ ለመገንባት ጥረት እየተደረገ በዚህ ሂደት ጠንካራ ኣቋም ያላቸው መንግስታዊ መዋቅሮችን መፍጠር ላይ ቀላል ያልሆነ ተግዳሮቶችና ችግሮች ባሉበት ወቀት ነው ለውጡና ሽግግሩ እየተካሄደ ያለው። ኣሁን ደግሞ በዚህ ባልጠነከረው የመንግሰት መዋቅር በጣም ብዙ የተደራረቡ ስራዎች በኣጭር ጊዜ ለመፈፀም እየተፈለገ ነው። መንግስተዊ መዋቅሩና ኣጠቃላይ የሃገራችን የፐለቲካ ስርኣት መዋቅር፤ እነዚህን ተደራራቢ ብዙ ስራዎች በኣጭር ጊዜ ተሸክሞ መፈፀም ይችላል ወይ ተብሎ መጠየቅ ያለበት ጉዳይ ይመስለናል።

ከዚህ ኣንፃርም ስናይ ኣሁን በሃገራችን ውስጥ ከዚህ ቀደም ሲደረጉ ከነበሩት ምርጫዎች ለየት ያለ ተኣኣማኒነት ያለው በኣግባቡ የተደራጀ የፖለቲካ ፍላጎቶቻችንን ከሞላ ጎደል ሊያሳካ የሚችል ምርጫ በህገመንግስቱ መሰረት ለማካሄድ የቀረን ጊዜ ኣንድ ኣመት ብቻ ነው። ለዚህ የሚደረገው ዝግጅት እጅግ ከፍተኛና ሁሉንም የመንግስት ኣካላትና የህበርተሰቡን ድጋፍና እንቅስቃሴ የሚጠይቅ ነው። ለዚህ የሚደረግ ዝግጅት ለምሳሌ የህዝብ ቆጠራ፤ ተፈናቃዮችን ወደ ነበሩበት የመመለስና ኑሮኣቸውን ማስተካከል፤ ሰላምና መረጋጋት ማስፈን፤ ኢኮኖሚው እንዲነቃቃ ማድረግ፤ የገዢው ፓርቲና የተቃዋሚ ፓርቲዎች የምርጫ ዝግጅትና እንቅስቃሴ፤ ለምረጫው በውጤት እንዲናወን መደረግ ያለበት ኣስተዳደራዊና ሎጅስካዊ ዝግጅት  ወዘተ እጅግ ብዙ ናቸው። እነዚህን በተገቢው መንገድ ማካሄድ የሽግግር ወቅቱ ዋነኛ ስራዎች መሆን ኣለባቸው። ከዚህ ኣልፎም የመንግስት የእለት ተእለት ተጨማሪ ስራዎችም ኣሉ። በዚህ ሁኔታ የፖለቲካ ቀውሱን የሚያባብሱ፤ ባልተደራጀና በሩጫ የሚሰሩ ስራዎች ከተጨመሩበት ውጤቱ ያማረ ኣይሆንም። ስለዚህ ግልፅ ሆነ የስራ ቅደም ተከተል ወጥቶ የሃገሪቱ የፖለቲካ መዋቅር ሊሸከም በሚችለው ሁኔታ እየተመዘነ ቢሰራና ፕሮግራም ቢወጣ የተሸለ ውጤት ይኖረዋል ብለን እናምናለን።

በማጠቃለል በሃገራችን ባለፉት 27 ኣመታት ዓለም የመሰከሩለት ከፍተኛ መህበራዊና ኢኮኖምያዊ ለውጦች የተመዘገቡና በዚህ መሰክ ውጤታማ የሆነ እንቅስቃሴ የተደረገ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ የፌደራል ስርኣቱ ኣሰኳል ከሆነው ከፖለቲካ ኣመራሩ በኩል የዲሞክራሲ ስርኣት ግንባታ ላይ ከፍተኛ ችግረች እንደነበሩ፤ ህገመንግስቱ በተግባር እየተጣሰ የቀየበት የኢኮኖሚውና ማህበራዊ ልማቱም

በፍትሃዊ ተጠቃሚነቱ ላይ ጥያቄና ጥርጣሬ እየተነሳበት የነበረ መሆኑ ይታወቃል። በእነዚህ ጥቄዎች መነሻነት ለውጥ የመጣበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን። በለውጡና በሽግግሩ ሂደት ደግሞ በርካታ የተወሳሰቡ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ፖለቲካዊ፤ አኢኖምያዊ፤ ፀጥታዎ ችግሮች እየተነሱ ኣጠቃላይ የፖለቲካ ስርዓቱን (ገዢው ፓረቲም ይሁን ቃዋሚዎች የሚያጠቃልል ነው) እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እየተጋፈጡ ያሉበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን። ይህ ሁኔታ ግልፅነት ያለው ሰትራተጅያዊ ኣቅጣጫና መዳረሻ ብቃት ያለው ኣመራር ይፈልጋል። ይህ ሰትራተጅያዊ ኣቅጠጫ በግልፅ ለህዝብ ቀርቦ ህዝብ ኣውቆትና እየተቸው በልፅጎ እንዲወጣ (የገዢው ፓርቲ የሁን የተቃዋሚዎች) ያስፈልጋል። ከዚህ ውጭ እንዲሁ በደመነብስ የሚደረግ እንቅስቃሴና የተወሰኑ የፖለቲካ ልሂቃን የእርስ በርስ መነታረክ ወይም መሰማማት ብቻውን እንደመፍተሄ መውሰድ ካሉን ችግሮች ጋር ኣይመጥንም ብለን እናምናለን።

በኣንድ ሃገር ያሉ የተለያዩ የፖለቲካ ኣማራጮች በሊህቃን ይጠነሰሳሉ ከዛ በኃላ ግን የፓርቲ ፕሮግራሞች ሆነው ህዝቡን ኣሳትፈው ተግባር ላይ ይውላሉ። የፖለቲካ ልዩነቶች በሰፊ ውይይትና ድርድር ይበለፅጋሉ ይዳብራሉ። በመጨረሻ ግን ልዩነቶቹ በግልፅ ወጥተው በህዝብ በምርጫ ውሳኔ ያገኛሉ። የዳበረው ሰላማዊውና ህጋዊ (ከጉልበት በመለስ) የሚደረግ የፖለቲካ ሽግግር መንገድ ይህ ነው። ኣሁን በፊታችን ተደቅኖ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ በተገቢው መንገድ ከተጠቀምንበት ሃገራችን ትክክለኛውን የዲሞክራሲያዊ ስርኣት ግንባታ ትጀምራለች። ይህ ደግሞ በሂደት በቀጣይ ምርጫዎች እየጎለበተ ይቀጥላል። ይህ ሲሆን ኣሁን ያለውን ሁኔታ ወደ ትልቅ ፀጋ መቀየር ይቻላል። ተመራጩም ይህ ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግልፅነት በጎደለው ሰትራተጅያዊ ኣመራጮች በሚገባ ተደራጅተው ለህዝብ ምርጫ ሳይቀርቡና ወጉ በማይታወቅ ሁኔታ ከቀጠለ ግን ውጤቱ ያማረ ኣይሆንም። በውጥና በሽግግር ውስጥ ኣለን እያልን ከመተማመኑ ይልቅ ጥርጣሬው እያየለ፤ ሰላምና መረጋጋት ጠፍቶ፤ ኢኮኖሚው እየሞተ ከቀጠለ ደግሞ፤ ሃገራችን ወደማትወጣው ኣዘቅት እንከታታለን ብለን እናምናለን። ያሉን ኣማራጮች እነዚህ ናቸው።

ኣሁን በሃገራችን ያለውን የፖለቲካ ቀውስ ለመፍታት ዋናው መንገድ ተኣማሚነት ያለው ምርጫ በህገመንግስቱ መሰረት ማካሄድ ነው። ይህ ሰላማዊ ህጋዊ ሽግግሩን ያጠናክራል። በሃገራችን ሊካሔድ እየታሰበ ያለው ምርጫ የሰላማዊና ህጋዊ ሽግግር ምርጫ በመሆኑ ክብደቱ ከፍተኛ ነው። ካዚህ በተጨማሪም እጅግ በጣም ኣሳሳቢ የሆነ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የሚደረግ ምርጫ በመሆኑ ሚዛኑ ከፍተኛ ነው። ይህንን ጉዳይ በኃላ ላይ ዘርዘር ኣድርገን እናየዋለን።

ከዛ በፊት ግን ምንም እንካን እስከኣሁን ድረስ የተገለፀው ሁኔታ ትግራይንም የሚመለከት ቢሆንም የቅርብ ጊዜ በሃገራችን የነበረውን እና እስለኣሁንም ድረስ ያለውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባትና

እኛም እንደግለሰቦች የዚሁ ብሄር ተወላጆች በመሆናችን የሚመለከተን ስለሆነ ትግራይ ውስጥ ያለውን ሁኔታ በተመለከተ ጥቂት ነገሮችን እንላለን።

## 2.2. ትግራይ ውስጥ ያለው ሁኔታ

በሃገር ደረጃ ሲዘረዘር የነበረው ፖለቲካዊ ሁኔታ ትግራይ ውስጥ የተለየ ኣይደለም። ህገመንግስቱ የሚያጎናፅፈውን መብቶች የትግራይ ህዝብም ሊጠቀምበት የሚችል ሁኔታ ኣልተፈጠረም። ህገ መንግስቱ ተግባር ላይ ይውል ኣልነበረም። ግን ደግሞ ለዚህ ህገመንግስት መመስረት ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል። ይህ በመሆኑም ለውጡ ከመምጣቱ እና ወደዚህ የሽግግር ምእራፍ ከመግባታችን በፊት ትግራይ ውስጥ በተለያዩ ኣከባቢዎች የህዝብ ሰላማዊ ተቃውሞ ነበር። የትግራይ ወጣቶች በማህበራዊ ሚድያው የለውጥ ፊታውራሪዎች ነበሩ። ስለ ለውጥ ፅፈዋል ታግለዋል። ለውጡ እንደመጣም የትግራይ ህዘብ በደስታ ነው የተቀበለው። ለውጡ በመጣ ማግስት የነበረው የህዝቡ ደስታ በግልፅ የታየና ከፍ ያለ ነበር። ከዚህም ጋር ጠቅላይ ሚኒስትር ኣብይ ኣህመድ ወደ ትግራይ ሄደው ባደረጉት የህዝብ ስብሰባ የተንፀባረቀው የደስታ ስሜት የዚህ ማሳያ ነው። በኃላ ላይ ግን ለረጅም ጊዜ ሆን ተብሎ ሲሰራበት የነበረው የጥላቻ ፖለቲካ (በጊዜው በቂ ምላሽ ይሰጠው ስላልነበረ) ከዚህ ጋርም ተያይዞ በተወገደው ኣስተዳደር ውስጥ በፌደራል ከፍተኛ የስልጣን ቦታዎች የነበሩት የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የህወሓት ኣባላት በስራ ላይ በነበሩበት ወቅት ኣደረጉት ለሚባለው ጥፋት የትግራይን ህዝብ በጠቅላላ በዛ ኣይን በሚመዝን የጥላቻ ፖለቲካ ተለውሶ የተካሄደው የመንጋ ፖለቲካ ህዝቡን በጠቅላላ ስጋት ውስጥ ከቶታል።

ይህ ጉዳይ በጥላቻ ንግግር ብቻ የቆመ ኣልነበረም። የትግራይ ተወላጆች በያሉበት ከፍተኛ የሂወትና የንብረት ጉዳት ደርሶባቸዋል። በርግጥ ይህ ክስተት በማንኛውም የሃገራችን ዜጎች በሃገር ደረጃ የደረሰ ከፍተኛ ጉዳት ነው። ኣሁን ግን የምንናገረው ስለትግራይ ነው። በትግራይ ተወላጆች ላይ ከደረሰው የኣካልና የማተርያል ጉዳት በተጨማሪ ከፍተኛ የስነኣምሮና በማንነታቸው እንዲሸማቀቁ ያለመ የፕሮፓጋንዳ ስራዎች ተሰርተዋል። ከነዚህ ጥቂቶቹን ለመግለጥ ያህል “ደርግ የወደቀው በኢህኣዴግ ትግል ሳይሆን በራሱ ነው” ከ60 ሽህ በላይ ሂወት ተከፍሎበት ለተመዘገው ለውጥ መስዋእትነቱ ለከፈለው ህብረተሰብ ይህ ኣባባል ትልቅ ቁስል ነው የሚፈጥረው። “የ27 አመታት የጨለማ ዘመን፣ የቀን ጅቦች፣ ፀጉረ ለወጥ በኣከባቢያችሁ ተከታተሉ”፣ ትግርኛ ተናጋሪ እየተባለ የተሰራው ዶኩመንታሪ ፊልም ወዘተ…፣ በትግራይና በኣማራ ክልል የሚያገናኝ መንገድ ተዘግቶ ንብረት እየተዘረፈ ፌደራል መንግስት ዝም ብሎ መቆየቱ፣ በኣቶ ኢሳያስና በዶክተር ኣብይ ሲደረግ የነበረው ትግራይን ያገለለ የሚመስል የተለያዩ ግንኙነቶች፣ በኣማራ ክልል እየተስፋፋ በመጣው የግዛት ይገባኛል ጥያቄና ይህንን ጉዳይ በሃይል ለመፍታት ዝግጅት የሚመስል ሰፊ የማስታጠቅና የማደራጀት እንቅስቃሴ፣ በትግራይ

ህዝብ ላይ እንደህዝብ ያነጣጠረ የጥቃት ዘመቻ” የህዝቡን ስጋት ከፍ ወዳለ ደረጃ ኣድርሶታል። የትግራይ ህዝብም ይህ ጉዳይ በጥቂት ጥፋት ሰርተዋል ተብለው በተጠረጠሩ የህወሓት መሪዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በትግራይ ህዝብ ህልውና፤ ማንነትና ክብር ላይ ያነጣጠረ ኣደጋ ነው የሚል ግንዛቤ ወስዶ ከዚህ ኣንፃር ተንቀሳቅሰዋል። ይህ ሁኔታ ሃገራዊ የፖለቲካ ቀውሱን ለመፍታት ኣስቸጋሪ ኣድርጎታል።

በሃገራችን ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሆን ተብሎ ሲሰራበት በቆየውና በለውጡ ዋዜማና ከለውጡ በኃላም እየተጠናከረ በመጣው በትግራይ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ የፖለቲካ ዘመቻ ኣንፃር የትግራይ ህዝብ ሌላውን ነገር ሁሉ ኣሳድረን ኣንድነታችንን ኣጠናክረን የመጣብንን ኣደጋ በጋራ ሆነን እንከላከል ማለቱ ተገቢ ነው። ሆኖም የትግራይ ህዝብ ኣንድነቱ ይበልጥ የሚጠነክረውና የሚመጣበትን ማንኛውንም ኣደጋ ከየትኛውም ኣቅጣጫ በብቃት መከላከል የሚችለው በውስጡ ያሉትን ፖለቲካዊ ችግሮች በመፍታት ለኣንድነቱና ውስጣዊ ጥንካሬው ደልዳላ መሰረት ሲኖረው ነው።

ትግራይ ውስጥ ኣሁን በጉልህ የሚታይ ሁኔታ ኣለ፤ በኣንድ በኩል ከትግራይ ውጭ ከመሃል ኣገር በተለይ ከኣማራ ክልል እና ከኤርትራ፤ በተናጠል ይሁን በቅንጅት ጥቃት ሊመጣብን ይችላል የሚል ስጋት ኣለ። ይህንን ሊመጣብን የሚችለውን ጥቃት በኣንድነት ቆመን እንመክት የሚል ኣስተሳሰብ ኣለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ጥቃትና በኣንድነት የመመከት ኣስፈላጊነት ተቀብሎ ግን ደግሞ ኣንድነታችን እንዲጠናከርና ዘላቂነትና ጠንካራ ፖለቲካዊ መሰረት እንዲኖረው በዋናነት የፖለቲካ ችግሮቻችንን በፍጥነት እየፈታን የበለጠ እንዘጋጅ የሚል አስተሳሰብ ኣለ። የዝግጅታችን ዋናው ትኩረት ፖለቲካዊ ችግሮቻችንን ፈጥነን በመፍታት ጠንካራ ፖለቲካዊ መሰረት ያለው ኣንድነት መገንባት መሆን ኣለበት። ከትግራይ ውጭ የሚመጣብንን ጥቃት በኣስተማማኝነት መመከት የምንችለውና ማንኛውንም ችግሮች መቋቋም የሚያስችለን በውስጣዊ ጥንካሬኣችን የሚመሰረተው በትግራይ ውስጥ ለራሳችን ብለን በምናደርገው ፖለቲካዊ ለውጥ መሆን ኣለበት። የዝግጅታችን ዋነኛው ባህሪ የሚለካው በርካታ ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን በተለም የተማረ ወጣት የህብረተሰብ ክፍል የህወሓት ኣባልና ደጋፊ ባለመሆኑ ብቻ ከፖለቲካዊ ስርኣቱና ከፍተኛ ኣስተዋፅኦ ሊያበረክት ከሚችልበት ስራ በማግለል ላይ የተመሰረተውን የፖለቲካ ምህዳር መቀየር መሆን ኣለበት። ከዚህ ጋር ደግሞ በሃገር ኣቀፍ ደረጃ የምናምንበት መርህ ላይ የተመሰረተ ስትራተጅያዊ ዝምድና በሃገራችን ካሉ የፖለቲካ ሃይሎች ጋር በመፍጠር ይህንን ማጠናከርና በሃገራችን ለሚደረገው የሃገረ መንግስት ግንባታ የራሳችንን ኣስተዋፅኦ ስናደርግ ነው።

ከላይ የተገለፀው ኣስተሳሰብ ለማሳካት ኣሁን በትግራይ ውስጥ የሚደረገው ለውጥ ሁሉን ኣሳታፊ የሆነ ጠንካራ ክልላዊ መንግስት በመመስረት ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል። ለውጡ ህወሓት እንደ የፖለቲካ ድርጅት ጠነከረም ደከመም የትግራይ ህዝብ ሁኔታ በህወሓት መዳከምና መጠንከር ብቻ የሚወሰን ወደማይሆንበት ደረጃ ማሸጋገር መሆን ኣለበት ይህ ደግሞ የሚሳካው መንግስትና የፖለቲካ

ድርጅት ሲለያዩ ነው። ተኣማኒነት ባለው ምርጫ ያሸነፈ የፖለቲካ ድርጅት ያሸነፈውን ያህል ስልጣን የሚጋራበት ህዝቡ የተለያዩ ኣማራጮችን እንዲቀርቡለት የሚያደርግ የክልሉ መንግስታዊ መዋቅር ተፈላጊውን ቅርፅ ይዞ (ህግ ኣውጭ፤ ህግ ተርጋሚ፤ ስራ ኣስፈፃሚ ሆኖ)፤ እነዚህ የመንግስት ኣካላት ኣንፃራዊ ነፃነታቸውን ጠብቀው ኣንዱ ሌላኛውን እየተቆጣጠረ መንግስት የህዝብን መብት የሚያስጠብቅለት ስርኣት መትከል ይገባል። ይህ ሲሆን ፍትህ ቀስ በቀስ ይረጋገጣል። ህዝብ ኣድልዎ የሌለበት ግልጋሎት ያገኛል። የመንግስትና የህዝብ ሃብት ብክነት በእጅጉ ይቀንሳል። መገናኛ ብዙሃን ኣንፃራዊ ነፃነት ይኖራቸዋል። በክልሉ ከመልካም ኣስተዳደር መጓደልና ኣድልዎ የሚመነጭ የፖለቲካ ኣለመረጋጋት ይቀንሳል። የህዝቡ ኣንድነት ይጠናከራል፡ ሰላም ይሰፍናል፤ የሃገር ውስጥ ይሁን የውጭ ኢንቨስትመንት ይበልጥ ይሳባል። ኢኮኖሚው ቀስ በቀስ እየተጠናከረ በማይታጠፍ መንገድ ያድጋል። ጠንካራ ክልላዊ መንግስት የመመስረት ጉዞኣችን በተሳካ ሁኔታ በተፈፀመ ልክ የፖለቲካ ልዩነቶች ችግር መሆናቸው ቀርቶ ፀጋ ይሆናሉ። ለኢኮኖምያዊ እድገትና ለሰላም መሰረት ይሆናሉ። ገዢው ፓርቲም በከፍተኛ የፖለቲካ እንቅስቃሴና ትግል ውስጥ ስለሚጠመድ ራሱን እየሞረደ ይበልጥ እየጠነከረ የተሻለ ኣመራር በመስጠት ኣሸንፎ ለመውጣት በሃሳብም በኣደረጃጀትም የበለጠ ብቃት እንዲኖረው በቀጣይነት ይዘጋጃል። ኣሁን እንዳለው በኣስተዳደራዊ መንገድ እየተቆጣጠሩ ስልጣን በመያዝ በስብሶ መቀመጥ ይቀራል። ይህንን ለማምጣት ለውጥ ያስፈልጋል።

በትግራይ የፖለቲካ ስርኣት ለውጥ የሚመጣው የትግራይን ህዝብ ጥቅምና መብቶችን መሰረት ኣድርጎ ከራሱ ከትግራይ ህዝብ ውስጥ ሲመነጭ ነው። ኣሁን ባለው ሁኔታ ከተለያዩ ኣቅጣጫዎች በገንዘብና በስልጣን ሃይል ከራሱ ከህዝቡ ያልበቀለና በህዝቡ ተቀባይነት የሌለው “ለውጥ” በህዝቡ ላይ ለመጫን የሚደረግ ሙከራ እንዳለ ይሰማል። ይህ በትግራይ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንደማይኖረው እንተማመናለን። ቀደም ብሎ እንደተገፀው ትግራይ ውስጥ ፖለቲካዊ ችግሮች ኣሉ። እነዚህ ፖለቲካዊ ችግሮች በውስጣችን ታግለን እንፈታቸዋለን። ከትግራይ ውጭ ባሉ ሃይሎች የስልጣንና የገንዘብ ማባበያነት በተፅእኖ የሚመጣ “ለውጥ” ግን የትግራይ ህዝብ በከፍተኛ ደረጃ ሊቃወም ይገባል። ምክንያቱም ከህዝብ ውስጥ የማይመጣ ከውጭ በተፅእኖ የሚመጣ ለውጥና ይህንን እናሳካለን የሚሉ “የለውጥ” ደላላዎች ሁሉ ጊዜ ከሁኔታዎች ጋራ በመለዋወጥ ቀጣይ ኣደጋ ውስጥ ስለሚከቱን ነው። ችግሮቻችንን ኣይፈቱም፤ ይልቅስ ይበልጥ ያባብሱታል፤ ለተጨማሪ የተወሳሰበ ችግር ያጋልጡናል። ስለዚህ የፖለቲካ ሂወታችንን ራሳችን መቆጣጠር ይኖርብናል። ከየትኛውም ኣቅጣጫ በስልጣን ይሁን በገንዘብ ኣማካኝነት ለውጥ ኣመጣለሁ የሚል ሃይል ነገ ገንዘቡ ወይም ስልጣኑ የሚሰጠው ሃይል ሲጠፋ ለሌላ ጌታ ያድራል። ጌታው እስካለ ድረስ ደግሞ የጌታውን በሽታ በሙሉ ይዞልን ይመጣል። ኪሳራው ከባድ ነው። በፅናት እንቃወመው። ማምጣት የምንፈልገውን ለውጥ ህዝባችን ያለምንም የውጭ ተፅእኖ ራሱ ታግሎ ማምጣት ኣለብት።

በመሃል ሃገር ከለወጡ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ የፖለቲካ ሁኔታ በትግራይ ህዝብ ላይ እንደህዝብ የህልውና ኣደጋውን ለመከላከል ኣንድነት ማጠናከር ተገቢ ነው ነገር ግን እኛ እየሞትን እየደማን ከሚገባን በላይ ከፍተኛ ዋጋ እየከፈልን የምንጠብቀውና የምንከላከለው የኢትዮጵያ ኣንድነት መኖር የለበትም የራሳችንን ጉዳይ ብቻ እንስራ የሚል ኣመለካከት በተለይ በወጣቱ ክፍል ጎልቶ መምጣት ጀምረዋል። ይህ የብሄርተኝነት ኣስተሳሰብ በመሃል ሃገር በተፈጠረ የጥላቻ ፖለቲካ የተገፋፋ ሆኖ ከዚህ በተጨማሪ ህወሓት ትግራይና የትግራይን ህዝብ የሚገባውን ትኩረት ኣልሰጠውም ከሚል ኣስተሳሰብም ይነሳል። ህወሓት ዋናው ስራውን ማሃል ሃገር ማልማት ላይ ብቻ በማድረግ ድርጅቱና የትግራይ ባለሃብቶችም ትግራይን ረስተው መሀል ሃገር እንዲሰፍሩ በማድረግ የትግራይን ህዝብ ከድተዋል ሃላፊነታቸውን ረስተዋል የሚል እሳቤም ይጨመርበታል።

ኣሁን የትግራይ ክልላዊ መንግስትና ህዝብ የሚያስተሳስረው ዋናው ጉዳይ የመጣብንን የህልውና ኣደጋ በጋራ ተባብረን እንከላከል፤ ሁለተኛው ደግሞ በከባድ መስዋእትነት በህገመንግስታዊ ስርኣት ያረጋገጥነውን መብት እናስጠብቅ፤ እንከላከል፤ በሚሉት ጉዳዮች ላይ ነው። ግን ደግሞ ህገመንግስቱ በተግባር ይጣስ ነበር ብቻ ሳይሆን አሁንም (መጠነኛ መሻሻል ያለ ቢሆንም) ትግራይ ውስጥ ህገመንግስቱ የሚፃረሩ ተግባራት እየተፈፀሙ ነው። ህወሓት ያልፈቀደው ኣስተሳሰብ በትግራይ መገናኛ ብዙሃን ኣይተላለፍም፤ የወረዳ የዞን ኣመራሮች የፓርላማ ኣባላት የቢሮ ሃላፊዎች ገሚሶቹ ተመራጮች ገሚሶቹ ተሸዋሚዎች ከህወሓት ፈቃድ ውጭ በመንግስት የስራ ሃላፊነት ኣይመደቡም ኣይመረጡም። እነዚህ የመንግስት ስራ ኣስፈፃሚዎች (ተሸዋሚዎች ይሁኑ ተመራጮች) ተጠሪነታቸው ለህወሓት ነው። እንደየመንግስት የስራ ሃላፊዎች ተጠሪነታቸውና የስራ ሃላፊነታቸው ሃላፊ ሆኖ በላያቸው ለተሾመ የመንግስት ባለስልጣን ወይም ለመረጣቸው ህዝብ መሆን ነበረበት። ኣሁን ባለው ልምድና ኣሰራር የሚሾም ብቃት ይኑረውም ኣይኑረውም የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ነው። ይህ ኣሰራር ደግሞ መንግስትና ፓርቲው እንዲለያዩ ካለማድረጉም በላይ በመንግስት ኣካላት መኖር የነበረበትን (check and balance) ያጠፋና በዲሞክራሲያዊ ማእከልነት እንዲተካ ያደርጋል። የህዝብ ተመራጮች ተጠሪነታቸው ለመረጣቸው ህዝብ መሆን ይቀርና ለፖለቲካ ድርጅቱ ይሆናል። ስለሆነም ችግሩ ስርዓታዊ (systemic) ነው። እንዲሁ ኣንዳንድ ነገሮችን በመነካካትና በሂስ ግለሂስ የሚሻሻል ኣይደለም።

ለምሳሌ የትግራይ የመገናኛ ብዙሃን ሃላፊ ሆኖ የሚሾም የመንግስት ባለስልጣን ለህወሓት ባለው ታማኝነት እየተመዘነ ወይም ደግሞ ባለው የኔትዎርክ መተሳሰር እየተመረጠ ነው። የሚበልጠው ጊዜ ደግሞ የድርጅቱ ማእከላይ ኮሚቴ የሆነ ሰው ነው። ይህ ሰው ማንም የሁን ማንም በዲሞክራስየዊ ማእከላዊነት እየተመራ የፓርቲ ታማኝነቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። የህዝቡ እሮሮ እና የተለያዩ ኣማራጭ ኣስተሳሰቦች “ጠላቶቹ ናቸው“። ስለዚህ በሙሉ ኣቅሙ ይዋጋቸዋል። በመሆኑም የኣስተሳሰብ ልዩነቶችን የሚያስተናግድና ህዝብ በመረጠው ኣስተሳሰብ ዙርያ እንዲሰባሰብ ኣይፈቅድም። ድርጅቱ

ያቀረበውን ሃሳብ ብቻ እንዲጋቱ ይታገላል። ኣስፈላጊ መስሎ ሲታየውም ኣስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ ችግር የመሰለውን ኣስተሳሰብ ማስወገድ ይፈልጋል። በአስተሳሰብና ኣሰራር ልእልና ማሸነፍ ከበድ ያለና ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ስለሚሆን ኣቋራጩን ይመርጣል።

በዚህ መንገድ የሚሰራ መንግስት የኣስተሳብ ልዩነትም እያለ ብዙሃኑ በመረጡት መንገድ የሚተዳደር የፖለቲካ ስርኣት ኣይገነባም። ሁሉም ህዝብ በተለያዩ ጉዳዮች ሁልጊዜ ተመሳሳይ ኣስተሳሰብ መያዝ ኣይችሉም። ማድረግ የሚቻለው የሃሳብ ልዩነቶችን በሰላማዊ ውይይት እውቀት ላይ ተመስርቶ ኣስተሳሰቡን በማብሰል መጨረሻም ብዙሃኑ ያመኑበትን ተግባር ላይ በማዋል ማጠናቀቅ ነው። ይህ በሃገር በክልል ደረጃ የተለያዩ ኣማራጮችን የሚያቀርቡ የፖለቲካ ቡድኖች በነፃ ሃሳባቸውን ለህዝብ ኣቅርበው የሚወዳደሩበት በነፃና ተኣማኒነት ባለው ምርጫ መቋጫ የሚያገኙበትን ኣሰራር ተግባራዊ በማድረግ ይፈታል። ኣሁን ትግራይ ውስጥ መካሄድ ያለበት ለውጥ ዲሞክራሲውን ማስፋትና የተስተካከለ ወደ ህዝብ የቀረበ የህዝብን ብሶት የሚሰማ መንግስት መመስረት ላይ ያተኮረ መሆን ኣለበት። እነዚህ በተደጋጋሚ የሚገለፁት የመልካም ኣስተዳደር መመዘኛዎች ቀስ በቀስ ግን በኣስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆኑት ዲሞክራሲው ሰፍቶ ወደ ህዝብ የቀረበና ለህዝብ ተጠሪ የሆነ መንግስት ሲመሰረትና ሲጠናከር ነው። ይህ ማለት ደግሞ ለምሳሌ ከስራ ኣስፈፃሚው ተነፃፃሪ ነፃነት ያለው የህግ ተርጋሚና ህግ ኣውጪ ሲኖር፣ ለህዝብ ወቅታዊና ፈጣን ግልጋሎት የሚሰጥ ቢሮክራሲ፣ ለህዝብ ተጠሪነት ያለው በህዝቡ በቀጥታ ወይም በወከላቸው ኣባላት የሚመረጥ የወረዳ ኣመራር፣ የከተማ ከንቲባ፣ የፓርላማ ኣባል ሲኖር ነው። በድርጅት የሚመደብ የወረዳ ኣመራር የከተማዎች ከንቲባ በድርጅት ምልመላ የሚመረጥ የፓርላማ ኣባል ተጠሪነቱ ለፖለቲካ ድርጅቱ እንጂ ለመረጠው ህዝብ ሊሆን ኣይችልም።

ህወሓትና በድርጅቱ የውስጥ ኣደረጃጀት መሰረት በስትራተጃዊ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ሃላፊነት የተሰጠው የህወሓት የፖለቲካና የድርጅት ቢሮ የትግራይ ህዝብ የወደፊት እድገት፣ ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ የሚጠናከርበት የሚሰፋበት ይበልጥ ህዝብን በሚጠቅም ስትረተጃዊ ኣቅጣጫ ጉዳዮች ላይ መጠመድ ነበረበት። ነገር ግን ዋነኛ የስራ ድርሻውን ትቶ የወረዳ የዞን ሃላፊዎች የፓርላማ ተመራጮች መመልመልና ማሰማራት ዋና ስራው ሆኗል። በነዚህ የእለት ተእለት ስራዎች (operational and administrative) ራሱን ይጠምድና ሰትራተጃዊ ጉዳዮችን ማሰብ ኣይችልም። እነዚህ ኣስተዳደራዊ ጉዳዮች ስልጣንህን በሰዎች ኑሩና ሂወት ላይ በመወሰን የምትጠቀምባቸው በሰዎች ኣይን ስልጣን የሚያጎናፅፉ ስለሆኑ ይመቻሉ። ከዚህ መውጣት ኣያስመኙም። ግን ደግሞ ይህ ኣሰራር ከህገመንግስቱ እምነትና ኣስተሳሰብ ውጭ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ የተሻለ ኣማራጭ እንዳይኖረውና (የኣስተሳሰብ፣የኣሰራር፣

የኣመራር ብቃት ያላቸው) ጠንካራ ሰዎች እንዳይወጡ እንደልጓም ሽብቦ የያዘ ኣሰራር ነው። ይህ በትግራይ ህዝብ ላይ የተጫነ ተልቅ ፖለቲካዊ ችግር ነው። ይህን ችግር ሊፈታው ይገባል።

የለውጡ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ወዲህ የህወሓት ኣመራሮች በተከላካይነት መንፈስ ነው ያሉት። በመጀመርያው ኣከባቢ ለምን እንደዚህ ሆነ ላይባል ይችላል፤ እስካሁን ድረስ ከማእከላይ መንግስት ይሁን ከሌሎች የተለያዩ ኣቅጣጫዎች ምን ይመጣብን ይሆን እያሉ ራሳቸውን ከማእከላይ መንግስት ፕሮግራሞችና ኣሰራሮች ያገለሉ በሚመስል ሁኔታ በተከላካይነት መቀመጥ ግን ፈጥኖ መለወጥ ያለበት ጉዳይ ነው። ይህ ሁኔታ በቅርቡ በህወሓት መእከላይ ኮሚቴ ስብሰባ ከተወሰኑ ውሳኔዎች ኣንፃር ስንነሳ እየተሻሻለ የመጣ ይመስላል። ይህ መሻሻል ተጠናክሮ መቀጠል ኣለበት እንላለን፤ መሻሻሉን ያየንባቸው ጉዳዮች በቀጣይ ሃገራዊ ምርጫ ላይ የተወሰደው ውሳኔ፤ በኢህኣዴግ ድርጅቶች ውህደት በተመለከተ ቅድመ ሁኔታውን መሰረት በማድረግ የተወሰነው ውሳኔ፤ በህገመንግስቱ መከበር ላይ ያለው ኣቃም፤ (ይህንን በኣርኣያነት በትግራይ ተግባራዊ ማድረግ የሚገባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) በሃገር ደረጃ ህገመንግስቱ ይከበር የሚለው ኣቃም በግልፅ ለህዝብ ይፋ ኣድርገዋል። በጥቅሉ ሲታይ ደግሞ በሃገሪቱ ኣሳሳቢ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ኣቃም በመውሰድ ይህ ህብረተሰቡ እንዲያውቀው በማድረግና ኣስፈላጊውን ትግል ለማድረግ መዘጋጀታቸውን ገልፀዋል። ይህ መጠናከር ያለበት ጅምር ነው እንላለን።

በዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጉዳይ የትግራይ ክልላዊ መንግስትና ገዢው ድርጅት ህወሓት ዋናው ስራቸው ትግራይን በተገቢው መንገድ መምራትና ማስተዳደር ነው። ይህ ማለት በትግራይ መልካም ኣስተዳደር ዲሞክራሲ፤ ሰላም ሰፍኖ በዚህ ሳብያ ደግሞ ጠንካራ ኢኮኖምያዊ ልማት እንዲመዘገብ ማስቻል ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ትግራይ የኢትዮጵያ ኣካል ስለሆነና በሃገራችን ኢትዮጵያ የሚደረገው ክፉም ይሁን በጎ ነገር ትግራይንም ስለሚመለከትና በትግራይም ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ስላለው፤ ህወሓትም እንደ ነባር ተሞክሮ ያለው ድርጅት የኣገራችንን የፖለቲካ ቀውስ በመፍታት ላይ የራሱ ድረሻ ስላለው፤ ገንቢ በሆነ መንገድ መሰተፍ ይገባዋል። ትግራይ ላይ ብቻ በመጠመድ የኢትዮጵያን ይቅርና የትግራይን ችግር መፍታት ኣይቻልም። ስለሆነም ህወሓት ኣሁን በሃገራችን በሚነሱ መሰረታዊ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚ፤ ፀጥታዊ ጉዳዮች ላይ ሃገራችን ከገባችበት ቀውስ ለመውጣት የሚያስችለን ስትራተጃዊ ኣቅጣጫና ኣተገባበሩ ላይ ጉልህ ኣስተዋፅኦ በማድረግ መሳተፍ ይኖርበታል። ይህንን ተሳትፎውንም ጊዜና ሁኔታውን ባገናዘበ መልኩ ኣስፈላጊ መስሎ ሲታየው ለኢትዮጵያ ህዝቦች ማሳወቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

3. <u>በሃገር ደረጃ ያሉን ኣማራጮች</u>

የሃገራችን ፖለቲካዊ ሁኔታ ኣሁን ከሚገኝበት ተነስተን ወደፊት ለመቀጠል ሁለት ኣማራጮች ያሉን ይመስለናል። ኣንደኛው ኣማራጭ ለውጡን በሃይል ከላይ ወደ ታች በመጫንና ኣሁን ስራ ላይ ያለውን ህገመንግስት ህገመንግሰታዊ ባልሆነ መንገድ የፖለቲካ ፍላጎትን ለማስፈፀም መሞከር ነው። ይህ ከተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎች በተለይ ደግሞ "ኣሃዱኣዊ ኣስተዳደር" ጂኦግራፊያዊ የፌደራል ኣከላለል እንከተላለን የሚል ፖለቲካዊ ኣስተሳሰብ ያላቸው የፖለቲካ ሃይሎች ይህንን ኣካሄድ የሚመርጡ ይመስላል። በሌላ በኩል ደግሞ  ኣሁን በስልጣን ላይ ያለው በኢህዴግ ድርጅታዊ ኣሰራር ወደ ስልጣን የመጣው ሃይልም ኣንዳንድ እርምጃዎቹና በተለያየ ጊዜ የሚሰጧቸው መግለጫዎች የዚህ ኣሰተሳሰብና ኣማራጭ ደጋፊ ይመስላል። ሁለተኛው ኣማራጭ ደግሞ እስከ ኣሁን ድረስ በስራ ላይ ያለውን ህገመንግስት በመከተልና ይህንን መሰረት በማድረግ በቀጣይ ምርጫ በሚረጋገጥ የህዝብ ፖለቲካዊ ፍላጎት መሰረት የህዝብ ውክልና (mandate) ይዞ ለውጡን ወደፊት መግፋት የሚል ነው። ይህንን ኣስተሳሰብ ኣሁን ያለውን ማንነት መሰረት ያደረገውን ፌደራላዊ ስርዓት የሚደግፉ ሃይሎች የሚጋሩት ኣስተሳሰብ ነው።

የመጀመርያውን አማራጭ የሚደግፉ ሃይሎች ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የመጣውን ለውጥ በሃይል በኣመፅ ኣምጥተነዋል የሚሉ ሃይሎች (በሃገር ውስጥ የነበሩ ይሁን ከሃገር ውጭ በለውጡ ወደ ሃገር የገቡ የፖለቲካ ሃይሎች) ኣሁን ያለው ለውጥ ህገመንግስቱን በመጠራረግ በሃይል ወይም ህገ መንግስታዊ ባልሆነ መንገድ የሽግግር ጊዜውን ማጠቃለል ይፈልጋሉ። የሚበልጡት የኦሮሞና ሌሎች ብሄረተኛ ድርጅቶች ኣቋማቸው ህገ መንግስታዊ ስርኣቱን ተከትሎ በህዝብ ምርጫ ለውጠን መደገፍ ወደሚለው ያመዘነ ይመስላል። ስለሆነም ህገ መንግስቱን ጠራርገን እናስወግድ በሚለው ኣስተሳሰብ ውስጥ የሚካተቱ ኣይመስልም።

ይህ ህገ መንግስቱን በመጣስ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት በሃገራችን እየተበራከቱ በመጡት ፅንፈኛ የብሄረተኛ ኣስተሳሰብ ባላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችም ይገፋበታል። እነዚህ ሃይሎች የ "ይዋጣልን" የፖለቲካ ኣስተሳሰብ በመከተል ሃገሪቱን ወደከፋ ችግረና ቀውስ ለመክተት የሚንቀሳቀሱ ይመስላል። በየኣከባቢው የሚነሱ ኣነስተኛ ችግሮችን ከማንነት ፖለቲካ ጋር በማያያዝ ችግሮችን የማባባስና የህብረተሰቡን ኣሰተሳሰብ በኣጭር ጊዜ የመመረዝ ችሎታ ኣላቸው። በመሆኑም እስከ ኣሁን ድረስ የፈጠሩት ችግር ይሁን ለወደፊትም የሚፈጥሩት ችግር ቀላል ኣይደለም። መነሻቻው ለየብቻ ቢሆንም እነዚህ "ኣሃዱኣዊ ኣስተዳደር" ፖለቲካ ኣራማጆችና ፅንፈኛ ብሄረተኞች ህገ መንግስቱን በመጣል ለውጥ ማምጣት ላይ ግን ይገናኛሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በዚሁ ህገ መንግስቱን በመጣስ ለወጥ ለማምጣት ላይ በኣቶ ኢሳያስ የሚመራው የኤርትራ መንግስትም ተመሳሳይ ኣቋምና የስራ እንቅስቃሴ ኣለው። ይህ የውጭ ሃይል ህገመንግስቱንና

በዚህ ህገ መንግስት የተቋቋሙትን ህገ መንግስቱን ለመተግበር የሚያስችሉትን የመንግስት ተቋማት በመጠራረግ ለውጥ በፍጥነት እንዲመጣ ይፈልጋሉ። ይህ ኣስተሳሰብ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ካላቸው "ቀና ፍላጎት" የሚነሳ ኣይደለም። የራሱን የኣቶ ኢሳያስን የስልጣን ዘመን ለማራዘም፤ የሀገረ ኤርትራ ግንባታ ፕሮጀክት ለማሳካት በማሰብ ነው።

ህገ መንግስቱን መሰረት ያላደረገ ይህንኑን የጣሰ የለውጥ ኣካሄድ ህጋዊና ሰላማዊ ፖለቲካ ለውጥ ማምጣት ኣያስችልም ብቻ ሳይሆን ሃገሪቱን እስከመበታተን ሊያደርስ የሚችል፤ ምን ሊያስከትል እንደሚችል መተንበይ የሚከብድ፤ ከማንኛውም ሃይል ቁጥጥር ውጭ የሆነ፤ ሁኔታ በመፍጠር ወደማንወጣው ኣዘቅት ይከተናል የሚል ኣስተሳሰብ ኣለን።

<u>ሁለተኛው ኣማራጭ፤</u> አሁን በስራ ላይ ያለውን ህገመንግስት መሰረት በማድረግ ቀስበቀስ ህጋዊና ሰላማዊ ለውጥ ማምጣት ሚፈልጉ ሃይሎች ናቸው። እነዚህ ሀይሎች በዚህ ጥቅል ኣስተሳሰብ ውስጥ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ቢሆንም በመሀከላቸው ልየነቶች የሉም ማለት ኣይደለም። የህገ መንግስቱ መሰረታዊ ይዘት ሂወቱ (soul) የሚባለው ዲሞክራስያዊ መሆኑን በመገንዘብ በህገመንግስቱ ያሉት የግለሰብ፤ የቡድን፤ የማህበረ ኤኮኖምያዊ መብቶች በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን፤ራስን በራስ ማስተዳደር የሚበለው አስተሳሰብ ደግሞ የክልሎቹ ኣቅም እስከፈቀደ ድረስ ህገመንግስቱን መሰረት ኣድረጎ ይህንን ሳይጥስ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን የሚፈልጉና ለዚህ የሚታገሉ ሃይሎች ኣሉ። እነዚህ ሃይሎች ይህ ከላይ የተገለፀው ሁኔታ መሰረት በማድረግ እንደሃገር ደግሞ የሃገራችንን ኣንድነትና ሃገራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ በመፈቃቀድና በእኩልነት የተመሰረተ ኣንድነትን የሚያጠናክር ሂደት እንዲበራታና፤ እንዲጠናከር ይፈልጋሉ። ህገመንግስቱን እንደከለላ እየተጠቀሙ ፀረ ዲሞክራሲ የሆነ ተግባራቸውን መቀጠል ሚፈልጉ ሃይሎችም ኣይታጡም። ዋናው ሃይል ግን የህገመንግስቱን መሰረታዊ ባህርይ (ዲሞክራሲያዊ መሆን) ጠብቆ ለውጡን በሰላማዊ ህጋዊ መንገድ ማስቀጠል የሚፈልገው ሃይል ነው። ከለውጡ በፊት የነበረው የፖለቲካ ኣስተዳደር ዋናው ችግር ደግሞ የፌደራል ስረዓቱ ዋነኛ ባህርይ የሆነው ዲሞክራሲያዊ የመሆን ይዘቱን ማጥፋት ነበር።

ይህንን መመለስ ይገባል። እንደተገለፀው የግለሰብ ሰብኣዊና ዲሞክራሲያዊ መብት መጠበቅ ኣለበት፤ የህዝቦች ብሄር ብሄረሰቦች፤ የክልል መሰተዳድሮች ስልጣናቸው ተጠብቆ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ መደረግ ኣለበት። የክልል መስተዳድሮች ህገመንግስቱን ተከትለውና ይህንን ጠብቀው እስከሄዱ ድረስ ጥፋት ቢሰሩም የራሳቸው ሃላፊነትና ከህዝብቸው ጋር ሆነው የሚያወራርዱት ሂሳብ መሆኑ ታውቆ ከጥፋታቸው እየተማሩ እንዲያስተካክሉ ዕድሉን መስጠት ይገባል። የህዝቦች በኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ መስኮች የመልማት መብታቸው የሃገሪቱ ኣቅም በፈቀደ መጠን በየጊዜው እየዳበረ የሚሄድ ሆኖ መጠበቅ ኣለብን። እነዚህን መብቶች የሚጥስ ኣካሄድ ድሮም ዘንድሮም ትክክል አይደለም መባል ኣለበት።

## 4. <u>የትኛው ኣማራጭ እንምረጥ</u>

ከላይ ሲዘረዝር ከመጣው ሃሳብ ግልፅ እንደሆነ የምንገምተው ኣሁን ባለው የሃገራችን ሁኔታ በስራ ላይ ያለውን ህገ መንግስት ተከትለን ይህንኑ መሰረት ኣድርገን ለውጡን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ እናስኬደው የሚለውን መንገድ ነው የምንመርጠው። ይህንን ስንል ይህንን ሃሳብ የማይቀበሉ ህገማንግሰቱን በሆነ መንገድ በመጣስ (ህዝባዊ ኣመፅ፤ በሌላም ህገመንግስታዊ ያልሆኑ ኣማራጮች) ለውጡን ማጠናቀቅ የሚፈልገሉ ሃይሎች እንዳሉ እናውቃለን። ይህ ብቻ ሳይሆን ኣሁን ያለው ትርክት በመንግሰት መገናኛ ብዙሃን ይሁን በማህበራዊ ሚድያ የበላይነት ያለው የኣሃዱኣዊ ሃገረ መንግስት ግንባታ ኣሰተሳሰብ ይመስላል።

እነዚህ ኣማራጭ ኣስተሳሰቦች ማለት ብሄር ብሄረሰቦችን መሰረት ያደረገው በማንነት ላይ የተመሰረተ የፌደራል ስርኣትና የኣሃዱኣዊ ሃገረ መንግስት ግንባታ ላይ መሰረት ያደረገው የፖለቲካ ስርኣት ግንባታ ኣሁን ብቅ ያሉ ኣማራጮች ኣይደሉም። በሃገራችን ሁለቱም የሃገረ መንግስት ግንባታ ኣስተሳሰቦች ተሞክረዋል። ኢህኣዴግ ስልጣን ከመቆጣጠሩ በፊት በሃገራችን የነበረው የሃገረ መንግሰት ግንባታ ኣካሄድ ኣሃዳዊ መንግስት የመገንባት ሂደት ነው የነበረው። ይህ በህዝቦች ኣመፅ ተወግደዋል። ቀጥሎም በኢህኣዴግ መሪነት ብሄር ብሄረሰብ መሰረት የደረገ የሃገረ መንግሰት ግንባታ ሂደት ተጀምሮ ኣሁን እደረስንበት ደረጃ ላይ እንገኛለን።

የእነዚህ ሁለት ኣማራጮች ደጋፊ የፖለቲካ ቡድኖች በከፍተኛ ደረጃ ሃሳባቸው ቀምረው ተደራጅተው ለህዝብ እንደ ኣማራጭ ቀርበው በሰላማዊ መንገድ ኣንዱ ኣሸንፎ ሌላውን ደግሞ ተቃዋሚ ሆኖ ተኣማኒነት ባለው ምርጫ እንድንሸጋገር መደረግ ኣለበት እንላለን። የኣሃዳዊ ሃገረ መንግስት ግንባታ ፖለቲካ ኣራማጆች የተበታተኑ ሃይሎች እንደሆኑ እናውቃለን። ግን በኣሰተሳሰባቸው የሚቀራረቡት ተሰባስበው ራሳቸውን ኣደራጅተው ሃሳባቸውን በሚችሉት ኣቅም ኣደራጅተው ለምርጫ ይዘጋጁ ይወዳደሩ። በማንነት ላይ የተመሰረተ ፌደራል ስርኣት ፖለቲካ ኣራማጆች ደግሞ እንደዚሁ ያድርጉ። በዚህ ሂደት የብዙ ሃይሎች መፈራረስ፤ መሰባሰብ (Realignment) ሊኖር እንደሚችል እንገምታለን። በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ የሽግግሩን መድረክ በውጤት ለመዝለቅ የሚያስችለው የተሻለውና በሃገራችን የሃገረ መንግስት ግንባታ ሂደት የፖለቲካ ስርዓቱን በህዝቦች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያስችለው ኣማራጭ ይህ ኣካሄድ ይመስለናል።

ይህንን በሃገራችን ያለውን የፖለቲካ ቀውስ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ መፍታት ከቻልን በሃገራችን እያንዣበበ ያለውን ኣደጋ እንከላከላለን፤ ሰላም እንዲሰፍን እናደርጋለን ብቻ ሳይሆን በሃገራችን ለዘመናት

በይደር የቆየውን የፖለቲካ ትራንፍርሜሽን ሂደት ለማካሄድ መሰረቱን እንጥላለን ማለት ይሆናል። ይህ ደግሞ እጅግ ከፍተኛ ስራና ውጤት ነው። ከዚህ በመነሳት ኣሁን ያለው የፖለቲካ ኣመራር ዋነኛ ስራው የተጀመረውን ለውጥ የፖለቲካ ትራንስፎሜሽን ለማምጣት በሚያስቸል መሰረት ላይ ማስቀመጥ ቢሆን ይመረጣል።

የፖለቲካ ትራንስፎሜሽን በግልፅ በተቀመጡ ግቦች ኣንፃር በማስቀመጥ ከእነዚህ ግቦች ዋናውና መሰረታዊው ጉዳይ ቀጣዩን ምርጫ በህገ መንግስቱ መሰረት ተኣማኒነት ባለው መንገድ በወቅቱ እንዲከናወንና ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ ሁሉም ዓይነት ዝግጅቶች መሰራት መሆን ኣለበት ብለን እናምናለን። ከዚህ ጋር ጎን ለጎን ኣሁን ያለው ገዢ ፓርቲ በህገ መንግስቱ በተሰጠው ስልጣን ብቻ እንዲወሰን፤ ማለትም ማንኛውም በስልጣን ላይ ያለ መንግስት የሚሰራቸውን የቀን ተቀን ስራዎች ሰላምና መረጋጋት እንዲከበር፤ ሁሉም ኣይነት የመንግስት ግልጋሎቶች ለዜጎች በተሟላ መንገድ መስጠትና ኢኮኖሚውን እንዲያንሰራራ ማድረግ ላይ ቢያተኩር ይመረጣል እንላለን።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎችም ዋናው ትኩረታቸው ከኣንድ ኣመት በኃላ ለሚደረገው ምርጫ ለማሸነፍ ሰፊ ሰላማዊ የፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ላይ ቢያተኩሩ። ይህ ማለት ራሳቸውን ማደራጀት፤ ማሰባሰብ፤ የምርጫ ማኒፌስቶ ማዘጋጀት፤ ሲመረጡ የሚሰሩትን ፕሮግራሞች በሰፊው በሰላማዊ መንገድ ለህዝብ ማቅረብ፤ ለዚህ የሚመጥን የሎጅስቲክስ ዝግጅት ማድረግ ላይ ቢያተኩሩ በሃገራችን ፖለቲካ ትራንፍርሜሽን ከፍተኛ ኣስተዋፅኦ ይኖራቸዋል። ይህ ሂደት በህዝቡ ላይ ተስፋ ኣጭሮ እንቅስቃሴው በሙሉ ወደ ሰላማዊ ፖለቲካዊ ውድድር እንዲያተኩር ግጭቶች፤ መፈናቅሎች፤ እንዲቆሙ፤ ሰላም እንዲሰፍን፤ ከፍተኛ ኣስተዋፅኦ የኖረዋል ብለን እናምናለን። ባጠቃላይ በቀረችን ኣንድ ኣመት ሃገራችንን መጠነ ሰፊ ወደ ሆነ የምርጫ ፖለቲካ ማእበል እናስገባት እንላለን።

## 5. <u>ቀጣይ እርምጃዎች (የፖለቲካ ፍኖተ ካርታ)</u>

### 5.1. ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን ማክበርና ማስከበር

ይህ ተግባር ኣሁን ያለውን ህገመንግሰታዊ ስርዓት መብታችን ያስጠብቅልናል የሚሉና በሃገራችን ሰላማዊና ህጋዊ ለውጥ ለማምጣት የሚፈልጉ ሃይሎች ሁሉ ሊፈፅሙት ይገባል። ኣሁን ባለው የሃገሪችን ሁኔታ የሀገረ መንግስት ግንባታ ሂደት በምን ኣይነት የፖለቲካ ኣስተሳሰብ መመስረት ኣለበት የሚለውን የፖለቲካ መሰረታዊ ኣቅጣጫ ላይ በግልፅ የወጣ ልዩነት እየታየ ባለበት ወቅት በማንነት ጉዳይ ላይ በተመሰረተ ዲሚክራስያዊ ፌደራላዊ ስርዓት የሃገረ መንግሰት ግንባታ የሚየምኑ ሃይሎች ሙሉ ኣቅማቸውን አሰተባብረው በመሀከላቸው ሁኔታው የሚጠይቀውን ዝምድናና ቅንጅት መስርተው በቀጣዩ ምርጫ ኣሸንፈው እንዲወጡ ሰፊ የዝግጅት ስራ ይጠይቃቸዋል። እነዚህ ሃይሎች ኣሁን

ተበታትነው በተናጠል ነው እየተንቀሳቀሱ ያሉት፡፡ ይህ ሁኔታ መለወጥ ኣለበት ከዚህ ኣንፃር ኣሁን ያለው ህገመንግስት ለህዝቦች የሚያጎናፅፈውን መብት በተገቢው መንገድ በመግለፅ ቀደም ብለው የተፈጠሩ ችግሮችና ድክመቶች እንዴት እንደሚታረሙ በማስቀመጥ ህገመንግስቱን እንደማሰባሰብያ ኣስተሳሰብ በመጠቀም ኣቅማቸውን ማሰባሰብ ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ ኣንፃር ገዢው ፓርቲ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ምርጫው ህገመንግስቱ በሚፈቅደው መሰረት ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ መወሰንና በዚሁ በውሳኔው መሰረት መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ግልፅ የሆነ ኣቋምና ውሳኔ ኣለማድረግ (በ default) ማለትም ውሳኔዎች በሁኔታዎች ኣስገዳጅነት እንዲደረግ መፍቀድ ሰላማዊና ህጋዊ የለውጥ ሂደት እንዳይኖር ሆን ብሎ እንደ መፍቀድ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎችም ይህንን ህገመንግሰታዊ ጉዳይ ተከትለው በቀጣዩ ምርጫ ሙሉ ዝግጅት እንዲያደርጉ መጋበዝ፡፡ ከህገመንግስቱ ውጭ የሆኑ በተለይ ደግሞ ከቀጣዩ ምርጫ ጋር በቀጥታ ያልተያያዙ ጉዳዮችን ከምርጫው በኃላ እንዲሰሩ ማቆየት፤ ይህ ኣስተሳሰብ በገዢው ፓርቲ ውስጥ ልዩነት የሚፈጥር ከሆነም ልዩነቱ በግልፅ ወጥቶ ኣንድ መልክ እንዲይዝ ማድረግ፡፡ በዚህ ሳብያም ፈጥኖ ለምርጫው በሚደርስ ሁኔታ የፖለቲካ ሃይሎች ኣደረጃጀት እንዲፈጠር ሁኔተዎችን ማመቻቸት፡፡ በሃሳቡ የማይሰማሙ የኢህኣዴግ ኣባል የፖለቲካ ድርጅቶች ካሉም ከኢህኣዴግ ውጭ ካሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ተቀናጅተው ራሳቸውን ለቀጣዩ ምርጫ ማዘጋጀት ስለሚችሉ፤ ኣንዳንድ ኣሁን እጅግ ኣሳሳቢና ኣንገብጋቢ እየሆኑ የመጡ ጥያቄዎች እንደ የኣዲስ ኣበባ ኣስተዳደር፤ የሲዳማ ክልል የመሆን ጥያቄ፤ የመሳሰሉ ህገመንግስቱን መሰረት ተደርጎ በህዝብ ምርጫ እንዲወሰን ማድረግ ሁኔታዎችን ፈጥኖ ማመቻቸት፡፡ እነዚህን የመሳሰሉትንና ሌሎች ጥያቀዎች ሊፈቱ የሚችሉበትን የውሳኔ ኣቅጣጫ ኣስቀምጦ ለህዘቡ ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ኣሁን ኣገሪቱን እየመራ ያለው ሃይል ዋና ስራው ህገመንግስቱን ማክበርና ማስከበር፤ በዚህ መሰረት ተኣማኒነት ያለው ምርጫ እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ ሰላም የህዝቦች መብትና ድህንነት ማስጠበቅ ማለትም የህግ የበላይነት እንዲከበር ማድረግ፤ ማንኛውም በሰላማዊ መንገድ በውድድር፤ በህዝብ ምርጫ የፐለቲካ ስልጣን መያዝ የሚፈልግ ሃይል ህግና ስርኣት ተከትሎ ያለምንም ተፅእኖ የሚወዳደርበት ከዚህ ውጭ በሃይል የሚደረግ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ግን እንደወንጀል እየታየ ተገቢውን እርምጃ የሚወሰድበት ሃገር ወደ ስርኣት ኣልበኝነት ሳትገባ በሰላማዊ ፖለቲካዊ ውድድር የሽግግሩን ወቅት የምናጠናቅቅበት ሁኔታ የመፍጠር ሃላፊነት ኣለበት፡፡

5.2. የቀጣዩን ሃገራዊ ምርጫ ተኣማኒነት ማረጋገጥ

ይህ በቀጣይ የሚደረግ ሃገራዊ ምርጫ በሃገራችን ታሪክ እጅግ በጣም ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። በተፈለገው ጥራትና ተኣማኒነት ከተካሄደ ደግሞ የሃገራችንን የፖለቲካ ስርኣት ሽግግር በተደላደለ መሰረት ላይ እንዲቀመጥ ማድረግ ያስችላል። ከዚህ የበለጠ ሌላ ፖለቲካዊ ተግባር ስለማይኖር በቀረን ኣንድ ኣመት ውስጥ በህገመንግስቱ መሰረት ውጤቱ ያማረ እንዲሆን ኣሁን በስልጣን ላይ ያለው ሃይልና ሌሎች የፖለቲካ ሃይሎች ለዚህ ውጤት መስራትና መዘጋጀት ኣለባቸው እንላለን። ይህ በሃገራችን ታሪክና የዲሞክራስያዊ ስርኣት ግንባታ እንደኣንድ ታሪካዊ ወቅት (milestone) ታሪካዊ ፍፃሜ የተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎች ፍላጎታቸውን ማሳክያ በማድረግ እንደገና ሃገሪቱን ችግር ውስጥ እንዳይከቷዋት መስራት ይኖርብናል።

ሃገራዊ ምርጫውን እንደ ቁልፍ ስራ በመውሰድና ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ ተኣማኒነት ያለው ምርጫ ከተካሄደ ከምርጫው በኃላ ምርጫውን ተከትሎ የሚመጣውንም ትርምስ ማስወገድ ወይም በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ያስችላል። ይህ ሂደት ከዚህ ቀደም በነበረው በልሹ ኣሰራር ምክንያት ጠፍቶ የነበረውን የሃገራችን የፖለቲካዊ ስርዓት ተኣማኒነቱን መመለስ ላይ ትልቅ ኣስተዋፅኦ ይኖረዋል። ኣሸናፊው ብቻ ሳይሆን የተሸነፈውም ሽንፈቱን በፀጋ ተቀብሎ የፓርላማ መቀመጫውን ይዞ ትግሉን እየቀጠለ ለሚቀጥለው ምርጫ ይዘጋጃል። ይህ ሁኔታ ህዝብ በመንግስት ላይ ያለውን እምነት በመጨመር ለተሻለ ሰላምና ኢኮኖምያዊ እድገት መነሻ ይሆናል።

በቀጣዩ ለሚደረገው ሃገራዊ ምርጫ በተገቢው መንገድ ለማካሄድ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ከወዲሁ መፈታት ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች ኣሉ። ከነዚህ ውስጥ ጎላ ጎላ ያሉትን ለመጥቀስ ተፈናቃዮች ወደቀያቸው ተመልሰው ሰላማዊ ኑሮኣቸው እንዲቀጠሉ ማድረግ፤ በሃገር ኣቀፍ ያለውን ያለመረጋጋት ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ማድረግ፤ የህዝብ ቆጠራ ማካሄድ ወይም በነበረው ምርጫው እንዲካሄድ መወሰን፤ የፖለቲካ ሃይሎች የምርጫ ሃሳባቸውን (ማኒፌስቶ) ኣዘጋጅተው በስፋት በሰላማዊ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ ማስቸል፤ ሰፊ የሆነ የምርጫ ኣደረጃጀትንና የሎጅስቲክስ ስራዎችን ማዘጋጀት የመሳሰሉ በርካታ ስራዎች ኣሉ። የመንግስትና የገዥው ፓርቲ ዋናው ትኩረትና ተቀዳሚ ተግባሩ ይህ መሆን ኣለበት። በጠቅላላ ሃገሪቱን ወደ ሰፊ የምርጫ ወቅት የፖለቲካ እንቅስቃሴ በማስገባት ፖለቲካዊ ሽግግሩን ባማረ ውጤት እንዲጠናቀቅ መስራት ኣለበት።

ይህ የምርጫ እንቅስቃሴ ትግራይም ውስጥ በሰፋት መካሄድ ይኖርበታል። በተለይ በድርጅታዊ ኣሰራር የድርጅት ካድሬ ብቻ እየተመለመለ ለፓርላማ ኣባልነት (ለክልል ወይም ሃገራዊ)፤ ለወረደ ኣስተዳዳሪነት፤ ለከተማ ከንቲባነት የሚደረገው ኣሰራር መቅረት ኣለበት። በየኣከባቢው ያለ ህዝብ

ከውስጡ ከነዋሪዎቹ የተሻለ ፍላጎቴን ይወክሉልኛል፣ኣስተሳሰቤን ይጋራሉ የሚላቸውን ተጠሪነታቸው ለመረጣቸው ህዝብና ኣከባቢ የሆነ የህዝብ ተወካዮች (የድርጅቱም ካድሬም ሊሆኑ ይችላሉ ህዝብ እስካመነባቸው ድረስ) እንዲመርጥ ሁኔታዎችና ኣሰራሩን ሊስተካከል ይገባል።

5.3. <u>የመንግስታዊ ተቃማት ተኣማኒነትን ማረጋገጥ</u>

በህዝብ ዘንድ ተኣማኒነት ያለው ምርጫ ማካሄድ ከብዙ ጠቀሜታዎቹ ኣንዱ የመንግስታዊ ተቃማትን ተኣማኒነት ከፍ እንዲል ማድረጉ ነው። በተጭበረበረ ምርጫ የሚመረጥና የስራ ኣስፈፃሚው ታዛዥ የሆነ የህግ ኣውጭ በህዝብ ዘንድ ተኣማኒ ሊሆን አይችልም። በስራ ኣስፈፃሚው መልካም ፍቃድ የሱ ታዛዥ በመሆኑ የሚቋቋም የፍትህ ስርኣት በህዝብ የታመነ የህዝብን መብት የሚያስጠብቅ የስራ ኣስፈፃሚውን የህግ ጥሰት የሚከላከል በህዝብ የሚከበርና ተኣማኒነት ያለው መሆን ኣይችልም። ተኣማኒነት ባለው ምርጫ የሚቋቋም ከተቃዋሚዎች በርከት ብለው የተወከሉበት የህግ ኣውጭ (ፓርላማ) ከተቋቋመ የስራ ኣስፈፃሚው ታዛዥ የመሆን እድሉ ይጠባል። ስለዚህ ለህግ ኣውጭ ተጠሪ የሆነ ከስራ ኣስፈፃሚው አንፃራዊ ነፃነት ያለው የህግ ተርጋሚ ደግሞ የተሻለ ስራ ኣስፈፃሚውን የመቆጣጠር ኣቅምና ፍላጎት ይኖረዋል። የኣንድ ፓርቲ የስልጣን ሞኖፖል ስለማይኖር። ይህ ደግሞ ቀስ በቀስ በተዋረድ የመንግስት ተቃማትን ተኣማኒነት እየዳበረ እንዲሄድ መሰረቱን ይጥላል። ያሁኑ ምርጫ በተገቢው መንገድ ከተመራ የተጀመረው ለውጥ ሰላማዊና ህጋዊ ይሆናል ብቻ ሳይሆን በሃገራችን ለሚደረገው የዲሞክራስያዊ ስርኣት ግንባታ ትልቅ መሰረት ይጣላል። የተረጋጋች ኢትዮጵያ እንድትኖር የጎላ ድርሻ ይኖረዋል።

ከነዚህ ከላይ የተገለፀው ተኣማኒነት ያለው ህገመንግስቱን መሰረት ያደረገ ዋነኛ ስራ ጎን ለጎን የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ለከፋ ኣደጋና ጉዳት እንዳይዳርገን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የሃገራችን ኢኮኖሚ ኣሁን ከደረሰበት ደረጃ በታች እንዳያሽቆለቁልና ትንሽም ቢሆን ነፍስ እንዲዘራ ለማድረግ ዋናው ስራ ሰላም የተረጋጋና ተስፋ የሚጣልበት ሊተነበይ የሚችል (predictable) የፖለቲካ ስርኣት እንዲኖር ማድረግ ነው። የህ ደግሞ ከለይ እንደተገለፀው ተኣማኒነት ያለው ምርጫ በማካሄድ ኣድርጎ የሚመጣ ትራንስፎርሜሽን እውን ይሆናል ብለን እናምናለን። ከዚህ ጋር ጎን ለጎን ከፖለቲካ ስራው ባልተናነሰ ሁኔታ የኢኮኖሚው ጉዳይ ራሱን የቻለ በከፍተኛ ትኩረት የሚመራ እንቅስቃሴ ያስፈልገዋል ብለን እናምናለን።

6. <u>ማጠቃለያ</u>

ሃገራችን በከፍተኛ የፖለቲካ ሽግግርና ቀውስ ውስጥ ትገኛለች። ይህ ሁኔታ የወቅቱ ሙቀት እያዩ በእለት ተእለት ስራና የጊዜውን ጥያቄዎች በማየትና ለመፍታት በመጠመድ ኣይፈታም እንላለን። ኣሁን

በሃገራችን እየታየ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ እንደከፍተኛ ፀጋና መልካም ኣጋጣሚ በመጠቀም የሃገራችንን ፖለቲካዊ ስርዓት ወደ ተደላደለ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለማሸጋገር እጅግ ሰፊ ዕድል ኣለ ብለን እናምናለን። ከዚህ ኣንፃር ስናየው መነሻ የምናደርጋቸው ታሳቢዎች ኣሉ። ኣንደኛው የኣንድ ሃገር ዲሞክራሲያዊ ስርኣት ግንባታ በኣንድ ምርጫ ብቻ ኣይፈፀምም። ማድረግ የሚቻለው ለቀጣይ እድገቱ መሰረቱን ማስቀመጥ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ መደረግ የሚችለው በሰላማዊ ህጋዊ መንገድ ብቻ ነው። በሃይል በጉልበት ወይም ህጋዊውን ኣሰራር በመጣስ ኣይመጣም።

መጪው ወቅቱን የጠበቀ ምርጫ በተመለከተ የተለያዩ ኣስተያየቶች እንሰማለን። የሃሳቦቹ ማጠንጠኛ በቂ ዝግጅት ኣድርገን ችግራችን ባስተማማኝነት የሚፈታ ተኣማኒነት ያለው ምርጫ ለማካሄድ ፖለቲካዊ ዝግጅት ያስፈልጋል፣ ለዚህ ደግሞ ጊዜ ይጠልቃል፣ ስለሆነም ምርጫው በተቀመጠለት ጊዜ ላይካሄድ ይችላል የሚል ነው። በሃገራችን ያሉትን የፖለቲካ ችግሮች በኣንድ ምርጫ ብቻ እንደሚፈቱ የሚያስብ ፖለቲከኛ ካለ የዋህ ይመስለናል። በኣንድ የምርጫ ወቅት ሊደረግ የሚችለው በተለይ እንደሃገራችን በመሰሉ በሽግግር ላይ ያሉ ሃገራት ውስጥ ቀጣይ የሚገነባው የዲሞክራስያዊ ስርኣት የሃገረ መንግስት ግንባታ በጠንካራ እያደገ የሚሄድ መሰረት ላይ ማስቀመጥ ብቻ ነው። ይህ ማለት ቀጣይነት ያለው ሰፊ ስራ እንዳለ በመገንዘብ የሃገሪቱ የፖለቲካ ሃይሎች በዋናነት የሚስማሙበት ጊዜው የፈቀደውን ያህል ተኣማኒነት ያለው በቀጣይነት ደግሞ እያደገ የሚሄድ የፖለቲካ ስርኣት ማስቀመጥ ላይ ያተኩራል ማለት ነው። ይህ ከሆነ ኣሁን የተሸነፈ የፖለቲካ ኣስተሳሰብ ራሱን ይበልጥ ኣደራጅቶ ከኣምስት ኣመት በኃላ ተወዳድሮ ሊያሸንፍ ይዘጋጃል ማለት ይሆናል።

በቂ ዝግጅት (የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የምርጫ ኮሚሽን ኣደረጃጀት፣ የምርጫ ስርኣት ዝርጋታ፣ ሰላምና መረጋጋት ኣለመኖር ወዘተ...) ተብሎ የምርጫ ጊዜውን ከህጉ ውጭ ማራዘም ህገ መንግስቱ የመጣስና ህገወጥ የመሆኛው ኣንድ መንገድ ነው። ይህ ደግሞ በራሱ ሁኔታ (በ default) የሚመጣ ከሆነ ኣሁን ልንጠቀምበት የምንችለውን መልካም ኣጋጣሚ በማሳጣት መገመት ወደማንችለው ውጥንቅጥ ሁኔታ ይከተናል። የምርጫ ዝግጅቶችን ሟሟላት በሃገር ደረጃ ስናየው በቁጥጥራችን ያለ ነገር ነው። ጉድለቶች ቢኖሩትም የሽግግር ምእራፉን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ያበቃናል። ይህ ስትራተጂያዊ ፍፃሜ ነው። ይህንን መልካም ኣጋጣሚ ተጠቅመን የተጓደሉብንን በቀረው ጊዜ ሟሟላት እንችላለን። ከዚህ ውጭ የሚኖር ኣማራጭ ግን ሁኔታዎች ከቁጥጥራችን ውጭ ሆነው እንደሃገር ልንወጣው ወደማንችል ኣዘቅት ሊከተን ይችላል ብለን እናእባለን።

ምርጫውን በተቀመጠለት ጊዜ ለማካሄድ ከወሰንን፣ በቀረን ኣንድ ዓመት ገደማ ሃገሪቱን ወደሰፊ “የምርጫ ፖለቲካ” ማለትም ሰላማዊና ህጋዊ ሰፋፊ የፖለቲካ ውይይት በማስገባት፣ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለፖለቲካዊ ስልጣንና ለቀጣይ የሃገረ መንግስት ግንባታ የራሱን ኣስተዋፅኦ የሚያደርግ ሃይልና

ሌላው በኣቋራጭ በግርግር ስልጣን ለመያዝ ሁሉንም ኣይነት መንገዶች (ህጋዊውንም፣ ህገወጡንም) መጠቀም የሚፈልግ ሃይል ለመለየትና በወጉ ለማስተዳደር ይመቻል። ይህ ደግሞ ሰላምና መረጋጋት የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ኣስተዋፅኦ ያደርጋል። የሃገሪቱ የወደፊት ጉዞና ኣቅጣጫ የሚተነበይ (predictable) ያደርገዋል። ይህ በኣለማቀፍ ግንኙነት ተኣማኒነትን በማትረፍ ለኢኮኖሚው መነቃቃት ኣስተዋፅኦ ይኖረዋል። የህዝቡንም በሰላማዊና ዲሞክራስያዊ መንገድ ያለ ተፅእኖ ፖለቲካ ምርጫውን እንዲያስተካክል፣ የፖለቲካ ንቃቱ ከፍ እንዲል፣ የሃገሩንና የራስን ፖለቲካዊ ሂወት ይበልጥ እንዲቆጣጣር ያስችለዋል። የሽግግር ሂደቱ በጠንካራ መሰረት እንዲገነባ ያስችላል።

በቀጣዩ ምርጫ ልናሳካው የምንመኘውና ማሰብ ያለብን ግብ የፖለቲካ ሽግግሩ <u>በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ</u> ለቀጣይ የሃገረ መንግስት ግንባታ ሰፊ መደላድል መፍጠር ላይ መሆን ኣለበት እንላለን። መቸም ኣሁን በሃገራችን የሆነ ምርጫ ሲደረግ የተጭበረበረ ኣንድ ፓርቲ ብቻ ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠረው ፓርላማ ይኖራል ብሎ መገመት ኣይቻልም። የተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎች በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ተመርጠው ፓርላማ ውስጥ መቀመጫ መያዛቸውና የሃገራችን ፓርላማ መሰረታዊ የሃገራችን የፖለቲካ ልዩነቶች ክርክር የሚደረግበት ህዝቡ ለቀጣይ የተለያዩ ኣማራጮችን የሚያይበትና የሚዘጋጅበት፣ መንግስትና ፓርቲ የሚለያዩበት፣ የመንግስት ዋነኛ ኣካላት (ፓርላማ፣ ህግ ተርጓሚውና ስራ ኣስፈፃሚው) ኣንፃራዊ ነፃነታቸውን ኣረጋግጠው በስራ ኣስፈፃሚው የማይታዘዙበት ሁኔታ በመፍጠር ቢጠቃለል እንኳን፣ ይህ ከቀጣይ ፖለቲካዊ ትራንስፎርማሽን ኣንፃር ከፍተኛ ውጤት ነው። ስለዚህ ለህጋዊው የፖለቲካ ሽግግር ተገቢውን ትኩረት እንስጥ እንላለን።

እናመሰግናለን፣